ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 002 መስከረም 2 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “ኢትዮጵያ በልጆቿ የተባበረ ክንድ እያሸነፈች እንደምትሻገር የመጣችበት መንገድ ማረጋገጫ ነው”

- ዶክተር ይልቃል ከፋለ
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በልጆቿ የተባበረ ክንድ እና ትግል እያሸነፈች እንደምትሻገረው የመጣችበት መንገድ ማረጋገጫ ነው ሲሉ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ተናገሩ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት "ሰላምና ደህንነት ስለኢትዮጵያ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ በባህርዳር ከተማ ባዘጋጀው 10ኛው የፓናል ውይይት ላይ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ክቡር ዶክተር ይልቃል እንደገለጹት፤ "ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች" የሚለው መሪ ቃል የረጅሙን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳይ ሃቅ ነው፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ እንዳሉት፤ ሀገራችን በየወቅቱ ከፍተኛ የአንድነት ስጋት ቢያጋጥምም እነዚህን ፈተናዎች ሁሉ በልጆቿ ብርታት በመሻገር ለዛሬ ደርሳለች፤ አሁንም ከውስጥና ከውጭ የተጋረጡባትን በርካታ ፈተናዎች ተቋቁማ ወደፊት መገስገሷን ቀጥላለች፡፡

ከፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ጥያቄዎች የሚመነጩ የደህንነት ስጋቶች ከተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በላይ ናቸው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ሆኖም እነዚህን ፈተናዎች ዛሬም ሆነ ነገ በተባበረ አንድነት እና ትግል እያሸነፈች እንደምትሻገር የመጣንበት መንገድ ማረጋገጫ ነው ብለዋል፡፡

ሰላም ምን ያክል ዋጋ እንዳለው፣ ደህንነት ለኢትዮጵያ ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነ በጥልቅ

“ኢትዮጵያ በልጆቿ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ትህነግ ከታጣቂዎች ፊት ያሰለፋቸው መነኩሴና ማየት የተሳናቸው አዛውንት

ሙሉቀን ታደገ





ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

ለአሸባሪው ሕወሓት ሰላም ክፉ ጠላቱ ነው፡፡ ይህ ቡድን ገና ከምስረታው ጀምሮ ስለሰላም አንድም ጊዜ አስቦ አያውቅም፡፡ ዘወትር ጠዋትና ማታ ስለትግል፤ ስለጦርነት እና ስለውግያ ማውራት እስኪያንገሽግሽ ድረስ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይሰብካል፤ በተግባርም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ መግደል፤ ማሰር፤ መዝረፍ፤ መድፈር፤ መገለጫዎቹ ናቸው፡፡

በቅርቡ እንኳን በአማራና አፋር ክልሎች ባደረጋቸው ተደጋጋሚ ወረራዎች በርካታ ጅምላ ጭፍጨፋዎችን መፈፀሙ ይታወሳል፡፡ ማይካድራን ጀምሮ የነጭና፣ ጋሊኮማ፣ ጭፍራና ሌሎች በርካታ የጅምላ ጭፍጨፋ ስፍራዎች ታሪክ የማይዘነጋቸው ናቸው፡፡

ቡድኑ ይህንን ሲያደርግ ታዲያ ምሽግ አድርጎ የሚጠቀምባቸው የትግራይ ነዋሪዎችም የችግሩ ሰለባዎች ናቸው፡፡ ቡድኑ ይህንን ሕዝብ እንደ ጋሻ እየተጠቀመ ከፊሉን ለጦርነት ከፊት ይማግዳል፤ ሌላውን ደግሞ ሀብትና ንብረቱን እየዘረፈ ለራሱ የጦርነት ሱስ ያውለዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ለእርዳታ የቀረበውን እንኳ በመዝረፍ ለጦርነት ከማዋል ወደኋላ የማይል ስለመሆኑ ሰሞኑን ከቡድኑ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሾልኮ የወጣው ሰነድ ያመላክታል፡፡

ግፍ መስራት የማይሰለቸው የሽብር ቡድኑ ዛሬ ላይ ደግሞ ሌላ አሳዛኝ ነገር አስመልክቶናል፡፡ ዋና የጥፋት ጦሩን ከኋላ በማድረግ አይነ ስውራን እና መነኮሳትን እንዲሁም ሕጻናትንና አዛውንትን በምብ አሸክሞ ከቀውጢው ውጊያ ፊት ለፊት አደረጋቸው፡፡ ጥምር ጦሩም ቀድሞውኑ የሽብር ቡድኑን ሴራ ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበር ከፊት ለፊት የተሰለፉት አይነ ስውራን ፣ መነኮሳት እንዲሁም ሕጻናት እና አዛውንቶችን እጅ እንዲሰጡ ጠየቃቸው፡፡ አብዛኞቹም ተገደው ነውና በዚህ ውስጥ የተገኙት በሰላም እጃቸውን ለመከላከያ ሰጥተዋል፡፡

ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ የዓለም ሕዝብ ይመልከትልን ዘንድ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ልሳን ይሁን ሲሉ አቤት አሉ፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ለጥምር ጦሩ እጃቸውን ከሰጡ ምርኮኞች መካከል የተወሰኑትን አነጋግሮ የሽብር ቡድኑ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ በወፍ በረር ያስመለከታቸኋል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ካነጋገራቸው ምርኮኞች

የምርኮኞቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ምስጢራዊ ሰነዱ ትህነግ ለራሱ ህልውና እንጂ ለትግራይ ሕዝብ ደንታ የሌለው መሆኑን አጋልጧል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የትህነግ እንቅስቃሴ የራሱን ፍላጎት እንጂ፤ የትግራይን ሕዝብ ጥቅምና መብት ለማስከበር ደንታ የሌለው መሆኑን ሰሞኑን ከቡድኑ ማዕከላዊ ኮሚቴ የወጣው ድብቅ ሰነድ በይፋ ማጋለጡን በባህር ዳር

ምስጢራዊ ሰነዱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ አጠናክሮ ቀጥሏል

መኣርግ ገ/እግዚአብሔር

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት የቀረበለትን የሰላም ጥሪ ወደጎን በመተውና ለትግራይ ሕዝብ የተላከውን እርዳታ ለራሱ ዓላማ ብቻ በማዋል በትግራይ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል አጠናክሮ መቀጠሉን የሚያሳይ መሆኑን በአራዳ ክፍለ ከተማ የትግራይ ብልፅግና ፓርቲ አመራር አቶ ሃይለ ገብረሚካኤል ተናገሩ። አቶ ሃይለ ገብረሚካኤል ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቆይታ

አሸባሪው ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ዜና

# ክልሎቹ 50 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የቁሳቁስ ድጋፍ ለሠራዊቱ አበረከቱ

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- የሲዳማና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ከማሕበረሰቡ ያሰባሰቡትን 49 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የዓይነትና ቁሳቁስ ድጋፍ ለአገር መከላከያ ሠራዊት የዓመት በዓል መዋያ አበረከቱ።

የሲዳማ ክልል የፓርቲ አደረጃጀት የዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ኤሊያሰ ድጋፉን ሲያስረከቡ እንደተናገሩት፣ የሲዳማ ክልል ሕዝብ ለአገር መከላከያ የዓመት በዓል መዋያ የሚውል የ25 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የዓይነትና ቁሳቁስ ድጋፍ አጭር ቀናት ውስጥ አሰባሰቦ ልኳል።

የሲዳማ ክልል ብቻውን ሶስት አምቡላንሶች፣ 200 ሰንጋ በሬዎች፣ ከ400 በላይ የበግና ፍየል ፣ 300 ኩንታል የስንዴ ዱቄት፣ ከ1200 ሊትር በላይ ዘይት፣ 285 ዩኒት የደም ፣ የምግብ ቁሳቁሶች የበሶ፣ የፓስታና መኮረኒ የዓይነትና ቁሳቁስ አድርጓል።

የሲዳማ ሕዝብ አሸባሪው ሕወሃት ለሶስተኛ ጊዜ የቃጣብንን ጥቃት ለመመከት ምንጊዜም ዝግጁ ነው ያሉት አቶ አሸናፊ፤ ከአገር መከላከያ ሠራዊት ጎን የትምና መቼም ይቆማል ብለዋል።

ሕዝቡ “እኛ እያለን ኢትዮጵያ በየትኛውም ኃይልና አሻጥር አትፈርሰም። ድጋፋችን ለኢትዮጵያ መቼም አይነጥፍም” ማለቱንም አቶ አሸናፊ ገልጸዋል።



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

በእለቱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በበኩሉ በሁለት ቀናት ውስጥ ከማሕበረሰቡ ያሰባሰበውን የ24 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የዓይነትና የቁሳቁስ ድጋፍ ለአገር መከላከያ ሠራዊት አበርክቷል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የፓርቲ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ አቶ በላይ ተሰማ በርክክቡ ወቅት ባደረጉት ንግግር፣ ለመከላከያ ሠራዊት የዓመት በዓል መዋያ ድጋፍን የክልሉ ሕዝብ  በሁለት ቀን ውስጥ አሰባስቦ ልኳል ብለዋል።

ድጋፉም 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ 438 ሰንጋዎች ፣ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የምግብ ቁሳቁሶች፣ ፓስታ፣ መኮረኒ፣ በሶ፣ ስንዴ ዱቄት፣ ዘይትና የመሳሰሉትን እንዳካተተ አቶ በላይ ተናግረዋል።

አቶ በላይ በርክክቡ እንደገለጹት፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሕዝቦች ለአገር መከላከያ ሠራዊት የሚደረገው ድጋፍ በዚህ አይቋጭም፤ የኢትዮጵያ ጠላት የሆኑትን ሁሉ ለመደምሰስ ከአገር መከላከያ ሠራዊት ጎን እንቆማለን፤ የኢትዮጵያ ሰላምና ብልጽግና እስኪረጋገጥ ድረስ እጃችን አይነጥፍም፣ አይናችን አይከደንም ማለታቸውን አመላክተዋል።

የአገር መከላከያ ሠራዊት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሊዊጂ በበኩላቸው፣ ክልሎቹ አዲስ ሁነው ቅድሚያ እራሳችንን እናቋቁም አላሉም። አገር እየተወረረች ቤትና እራስን ማቋቋም አንችልም ብለው ላደረጉት ድጋፍ ክልሎቹን አመስግነዋል።

እንደ አገርም የኢትዮጵያን ሰላምና ብልጽግና ለማረጋገጥ በሁሉም ልማታዊና የደህንነት ስራዎች በጋራ መቆም እንደሚገባ የተናገሩት ወይዘሮ ማርታ፣ እንዲህ ካበርን የኢትዮጵያና የሕዝቦቿ ጠላት የሆኑትን ድህነትን፣ ኋላቀርነትን፣ እና ሌሎች የሕዝቦች ጫንቃ ላይ የወደቁ ጫናዎችን በአጭር ጊዜ እናስወግዳለን።

ለሁሉም አገራዊ ስኬቶቻችን አንድነታችን በሁሉም አገራዊ ጉዳዮች ሊቀጥልና ሊጠናከር ይገባዋል ሲሉም ወይዘሮ ማርታ አክለው ተናግረዋል።

# የምርምር ውጤቶች ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ተቋማት ተቀናጅተው ሊሰሩ ይገባል

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰሩ ጥናቶች ማሕበረሰቡ ላይ ተግባራዊ ሆነው ውጤት እንዲያመጡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ ተገለጸ።

14ኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ኮንፈረንስ በአድማስ ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት በተካሄደበት ወቅት የአድማስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት እና የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማሕበር ፕሬዚደንት ዶክተር ሞላ ፀጋዬ እንደተናሩት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚወጡ ተማሪዎች የማህበረሰቡን ችግሮች መፍታት የሚያስችሉ የምርምር ስራዎች ላይ ትኩረት በመስጠት መስራት አለባቸው።

ዶክተር ሞላ፣ አድማስ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት 13 ዓመታት በተለያዩ ወቅታዊ አገራዊ ይዘት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ዓመታዊ እና አገራዊ የጥናት ኮንፈረንሶች መካሄዳቸውን አስታውሰው በዚህ ዓመት የአፍሪካ ቀንድን ያካተቱ የምርምርና ጥናቶች ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ኢንዲደርሱ እና ከመማር ማስተማሩ በዘለለ ለማሕበረሰቡ ተግባራዊ ስራዎች እንዲሰሩ ታሳቢ የተደረገ ነው ብለዋል።

የትምህርት ጥራትና የመመሪያ ጥሰቶች ዙሪያ በተለያዩ ብዙሃን መገናኛዎች ጭምር ይነሳል  ያሉት ዶክተር ጸጋዬ የትምህርት ጥራት ከጥሰት በላይ ነው ብለዋል።

የትምህርት ጥራት ተቋማት ተማሪዎችን ተቀብለው አብቅተው እና ወጥተው ስራ እስከመያዝ እና ስራ እስከመፍጠር ደርሰው ለአገር እና ለማህበረሰብ አስተዋጽኦ እስከማድረግ የሚደርስ ረጅም ጊዜ ውጤት ማሳያ መሆኑን ባገናዘበ መልኩ በስፋት መታየት እንዳለበት ጠቁመዋል።



ዶክተር ኤባ ሚጄና





አቶ ተስፋዬ ዘውገ





ዶክተር ሞላ ፀጋዬ

ጥሰት ሲኖር መታረም አለበት ያሉት ዶክተር ሞላ፤ የትምህርት ጥራት የሚረጋገጠው ስለጥሰቶች ስለተወራ ብቻ ሳይሆን መምህሩም፣ ዩኒቨርሲቲውም ወላጆቹም በጋራ መስራት ሲችሉ ነው ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ጥራት እንዲያመጡ ከመንግሥት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መስራት የሚገባ ቢሆንም ከዚያ ባሻገር የብዙሃን መገናኛ እና ሌሎችም በጋራ ሆነው ሊሰሩበት የሚገባ ነው። ነገር ግን የአሉባልታና የሰሚ ሰሚ ጉዳዮች በዚያው ልክ ሊታረሙ ይገባል ሲሉም ጠቁመዋል።

ጥናትና ምርምር ዓላማ ችግር መፍታት በመሆኑ በአካባቢያችን ያሉ ሰፊ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ተጨማሪ እውቀቶችን ለማዳበር ጥናት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የአካዳሚክ ጉዳዮች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤባ ሚጄና በበኩላቸው፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመውጫ ፈተና ላይ ጥናታቸውን አቅርበዋል።

የሚቀርቡ ጥናቶችም ሆኑ በዩኒቨርሲቲዎች የሚደረጉ ጥናቶች ማህበረሰቡ ላይ ተግባራዊ ሆነው ውጤት እንዲያመጡ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል ወደ ስራ በመተርጎም ሊሰራበት እንደሚገባ ገልጸዋል።

በመውጫ ፈተና እና ኢንተርንሺፕ ጥናቶች የሚገኙ ግብዓቶች በየሴክተሩ ለሚደረጉ መሻሻሎች ጠቀሜታቸው ከፍ ያለ ነው ብለዋል።

ጥናቶች በሸልፍ ላይ የሚቀመጡ ብቻ ሳይሆን ለህብረተሰቡ ተደራሽ የሚሆኑበት እና ስራ ላይ የሚውሉበት አጋጣሚ አንዱ የተለያዩ ኮንፈረንሶች ሲቀርቡና በብዙሃን መገናኛው ጭምር ሲተላለፉ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

የምስራቅ አፍሪካ አገራት አብረው የሚኖሩ እና አብረው የሚሰሩ በመሆኑ በጋራ የመለወጥ እና የአኗኗር ዘይቤ አብሮ የማሳደግ እና የመለወጥ እድል ስላለው ጥናቶች ሲደረጉ ልምድ የመለዋወጥ ባህል በቀጣይነት ሊሰራበት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በአድማስ ዩኒቨርሲቲ የሀርጌሳ ቅርንጫፍ ፕሬዚደንት አቶ ተስፋዬ ዘውገ በበኩላቸው ከተለያየ ዘርፍ የመጡ ባለሙያዎች የየራሳቸውን የምርምር ውጤቶች ለሕዝብ ሲያቀርቡ የየራሳቸው በጎ ሚና አላቸው ብለዋል። በአገራችን በመቶ ሺዎች የሞቆጠሩ ተማሪዎች የሚሰሯቸው ጥናቶች እና ምርምሮች በማህበረሰቡ ትርጉም ያላቸው ችግሮችን ሊፈቱ እንደሚገባ ገልጸዋል።

አቶ ተስፋዬ በሶማሊ ላንድ የህብረተሰቡን አገር በቀል እውቀት በመጠቀም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሥራዎችን በሠላማዊ ሁኔታ ማስኬዳቸው ለሌሎች አርአያ ሊሆን የሚችል መሆኑን መታበዘባቸውን ገልጸዋል።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በየደረጃው የሚደረጉ ጥናቶች የህብረተሰብን ችግር የሚፈቱ እንዲሆኑ በመንግሽት ሆነ በተለያዩ ተቋማት በኩል ጥቆማዎች ሊሰጡ እንደሚገባ ገልጸዋል።

# ኢትዮጵያ ፈተናዎችን በአሸናፊነት እንድትሻገር አገልግሎቱ ብርቱ ጉልበት ሆኗል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው ዓመት ባከናወናቸው የሪፎርም ሥራዎች ዘመኑን የሚዋጁ ቴክኖሎጂዎች በመታጠቁና የላቀ ብቃት ያለው የሰው ኃይል አቅም በመገንባቱ ኢትዮጵያ ፈተናዎችን በአሸናፊነትና በጽናት እንድትሻገር ብርቱ ጉልበት መሆኑን የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል ተመስገን ጥሩነህ ለመላው ኢትዮጵያውያን ባስተላለፉት የአዲስ ዓመት የመልካም ምኞት መልዕክት እንደጠቆሙት መጪው አዲስ ዘመን ለኢትዮጵያውያን ሰላም፣ መቻቻል፣ መከባበርና መፈቃቀድ የሰፈነበት እንዲሆን ተመኝተዋል፡፡የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት እና ጥቅም እንዲረጋገጥም ሁሉም ተባብሮ እና ተደማምጦ የሚሰራበት እንዲሆንም አሳስበዋል።

የተቋሙ አባላት የሥጋት ቀጣና በሆኑ አውደ ውጊያዎች ጭምር በመሠማራት መረጃ በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ለሚፈለገው ዓላማ እንዲውል በማድረግ ሀገራዊ ግዳጃቸውን እየተወጡ በመሆኑ አክብሮቴና የአዲሱ ዘመን መልካም ምኞቴ በያሉበት ይድረሳቸው ብለዋል፡።

‹‹መላው ኢትዮጵያውያን እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ። አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤናና የስኬት እንዲሆን በራሴ እንዲሁም በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አመራሮች እና ሠራተኞች ስም መግለጽ እወዳለሁ›› ያሉት አቶ ተመስገን፤ በተለይ የኢትዮጵያን ህልውና ለማረጋገጥ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በግዳጅ ላይ የምትገኙ የጀግናው የመከላከያ ሠራዊት እና የጥምር ጦሩ አባላት መላው ሕዝብ የሰላም አየር እንዲተነፍስ የሕይወት ዋጋ ጭምር እየከፈላችሁ በመሆኑ ክብር ይገባችኋል ብለዋል፡፡

‹‹ውድ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች አዲሱ ዓመት ለሰላም በምትከፍሉት መስዋዕትነት በአዳዲስ የድል ብሥራቶች የሚታጀብ እንደሚሆን በልበ ሙሉነት እገልጻለሁ፡።እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ ብለዋ አቶ ተመስገን፡፡

በመልዕክታቸው ኢትዮጵያ ሰላምን አበክራ ትሻለች። የሰላሙ መንገድ ዛሬም ክፍት ነው። ይህን ባለመቀበል ጦርነትን የቀሰቀሱ አካላት ዛሬም የሰላምን ዋጋ ተረድተው በአዲስ ዓመት በአዲስ መንገድ እንዲጓዙ ኢትዮጵያ ጥሪ ታቀርባለች ያሉት አቶ ተመስገን፤ በሀገር ህልውና የተቃጣውን ጥቃት ጀግናው የመከላከያ ሠራዊትና የጥምር ጦሩ በብቃት መመከታቸውንና ወደፊትም ይህ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡



አቶ ተመስገን ጥሩነህ


# ትናንት ካሳለፍነው አሉታዊ ነገሮች ይልቅ ነገ ልጆቻችን ጥላቻ እንዳይወርሱ እርቅ መፈጠር አለበት

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፦ በአዲሱ ዘመን ትናንት ካሳለፍናቸው አሉታዊ ነገሮች ይልቅ ነገ ልጆቻችን ጥላቻ እና በደል እንዳይወርሱ በአገር ደረጃ እርቅ መፈጠር እንዳለበት የቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርስቲ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚደንት ቄሲስ ዶክተር መዝገቡ ካሳ አሳሰቡ፡፡

ቄሲስ ዶክተር መዝገቡ ካሳ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፣ በአዲሱ ዓመት የተሻለ ዘመን እንዲመጣ እንደ አገር መግባባትና እርቅ ያስፈልጋል። ትናንት ካሳለፍናቸው አሉታዊ ነገሮች ይልቅ ነገ ልጆቻችን ጥላቻ እና በደል እንዳይወርሱ በአገር ደረጃ እርቅ መፈጠር አለበት፡፡

በ2014 ዓ.ም የሚያሳዝኑና ልብ የሚሰብሩ ነገሮች ቢኖሩም መልካም እና ጥሩ አጋጣሚዎች ነበሩ ያሉት ቄሲስ መዝገቡ፤ አዲሱ ዓመት 2015 ዓ.ም የገባንበት ችግር የሚቀረፍበት፣ የተሳሰርንበት መልካም እሴት የሚጎለብትበት፣ በጎ ስራ የምንሰራበት ክፉውን የምናርቅበት፣ ጤናማ እና ሰላማዊ ግንኙነት የምንፈጥርበት፣ ትናንትና የመጣንበትን መንገድ በማረም እና መልካም ነገሮችን በመትከል የምናሳከበት ዘመን መሆን አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።



ቄሲስ ዶክተር መዝገቡ ካሳ

አሮጌውን ዘመን ሸኝተን አዲስ ዘመን ስንቀበል ዘመኑን መልካም የሚያደርገው የቁጥር መለዋወጥ ብቻ ሳይሆን የመሰረታዊ ማንነት መለወጥን አብሮ ይዞ መሆን አለበት ያሉት የሃይማኖት አባቱ፤ የምንፈልጋቸው መልካም ነገሮች እውን የሚሆኑት በምናደርገው የስራ ክንውን ከሰዎች ጋር በሚኖረን ጤናማ ግንኙነት ነው ብለዋል።

በአሮጌው ዓመት አካላቸውን ያጡ፣ ደማቸው የፈሰሰ፣ ልባቸው የተሰበረ የሚወዷቸውን ወገኖች ያጡ፣ በቁጭት፣ በጥላቻ እና በቂም ያሉበትን ሁኔታ በእርቅ መፍታት ካልተቻለ ሌላው ደግሞ በተራው ወደ መበደል እንዳይሸጋገር አገራዊ እርቅ ያሻልም ብለዋል።

ዶክተር ቄሲስ መዝገቡ፣ እንደ ክርስትና እምነት ንሰሃ የማይሰርዘው ሀጢያት የለም፤ እንደ ማህበረሰብ ደግሞ ይቅርታ የማይሸፍነው በደል የለም፤ ስለዚህ ከልብ እና ከእውነት አገራዊ በሆነ ደረጃ እርቅ ያስፈልጋል ሲሉም አጽንዖት ሰጥተዋል።

በቀጣይም የተሻለ ዘመን ለማምጣት የተጎዱ የቆሰሉ የልብ ስብራት የደረሰባቸው የተበደሉ ሁሉ ይቅር የሚባባሉበት በአገር ደረጃ እርቅ ያስፈልጋል ብለዋል።

በተግባቦት አንዱ በአንዱ ጫማ ውስጥ ሆኖ ማየት እንዲችል በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባቦት አስፈላጊ መሆኑንም ጠቁመዋል።

መንግሥት ማህበረሰቡን በኢኮኖሚ በማህበረሰባዊ ሁኔታዎች አዎንታዊ ውጤት እንዲያመጣ ሰፊ ድርሻ እንዳለው አስገንዝበዋል።

መንግሥት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ ህይወት፣ በህግ፣ በስነምህዳሩ ላይ እውነታውን በግልጽ ለይቶ የህዝቡን ፍላጎቶች ለማሳካት በታማኝነት፣ በተጠያቂነትና በኃላፊነት፣ በትጋት መስራት ይኖርበታል። የህዝቡን ስሜት እና ፍላጎት ማዳመጥ ከተቻለ ችግሩንም መልካሙንም አብሮ መጋራት ይቻላል ብለዋል።

የነገዋን መልካም ኢትዮጵያን ለመገንባት መንግሥት፣ ቤተሰብ፣ የትምህርት ተቋማት፣ ማህበራዊ ተቋማት ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑንም ገልጸው፤ በተለይ ወጣቱና አምራቹ የህብረተሰብ ክፍል በአገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ላይ በጎ ሚናዎች መወጣት አለበት ሲሉም አሳስበዋል። ወጣቱ አሉታዊ እና አፍራሽ አቅጣጫዎችን ባለመከተል በአገር ደረጃ የሚደርሰውን ከፍተኛ ጉዳት ማስቀረት እንደሚገባውም መክረዋል።

የሰውነታችን የስሜት ህዋሳት የየራሳቸው ሚና እንዳላቸው ሁሉ ሁሉም ማህበረሰባችን እኩል ዋጋ፣ ክብርና ማንነት እንዳለው የምንረዳበት እይታ በማምጣት ምሉዕነታችንን ወደ መረዳት ማምጣት አለብን፣ በዚህ ረገድ ተግባቦት ካለ ከባድ የሚባሉ መጪው ጊዜዎች ሁሉ ቀላል ይሆናሉ ብለዋል።

እንደ ቄሲስ ዶክተር መዝገቡ ቤተሰብ ትንሹ የአገር መገለጫ ነው። እንደ አገር መፍረስ ማለት የቤተሰብ፣ የጎረቤት መፍረስን ብሎም አገር ላይ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ሰው ተኮር ስራዎች ትኩረት ያስፈልጋቸዋል።

የሁሉም ሃይማኖቶች አስተምህሮ መልካምነትንና በጎነትን እንጂ ጥላቻና ጠብን የሚያስተምሩ ባለመሆናቸው የልዩነት ግንብ መኖር የለበትም፤ ትውልዱ የሃይማኖት ትምህርትን ጨምሮ የሥነምግባር ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ሊሰጥ የሚገባ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ሥነምግባር በኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አለመካተቱ ልጆች በጎነትን፣ ቅንነትን፣ ደግነትን፣ መልካምነትን፣ የሰዎች ሃሳብን መረዳት፣ ያላቸውን መስጠት መለገስ፣ በመስጠት መክበር በመመጽወት ውስጥ ባለጸግነት እንዳለ እየተረዱ እና እየሰሙ ካደጉ ወንድምን ለመግደል የሚሰለፍ አይኖርም ብለዋል።


ላለፉት 50 ዓመታት በላይ የጥላቻው እና ጦርነትን ያየን በመሆኑ አሁን በመግባባት፣ በፍቅር መስራት፣ በወንድማማችነት መኖር፣ ቀናነት እና መልካምነት እንደ አገር፣ እንደ ማህበረሰብ፣ እንደ ፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት የት እንደሚያደርሰን ለማየት ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል።

አካል ለማደግ ውሃ እና ምግብ፣ አእምሮ ለማደግ ትምህርት እንዲሁም ለመንፈሳዊ የሰዋዊ የማንነት ትርጉም የሚገኝበት በመሆኑ አካላዊ፣ አእምሯዊ እና መንፈሳዊ እድገትን ያጣመረ እድገት ያስፈልጋል። ሰው አካላዊ ፣ አዕምሯዊ እና መንፈሳዊ እድገት ሲኖረው ሙሉ ዕድገት ያገኛል ሲሉም አስገንዝበዋል፡፡

ከራስ ወዳድነትና ጥቅመኝነት በመውጣት ወደ በጎ የሚሻገር ማንነት ከትምህርት ጋር አብሮ ማደግ እንደሚገባውም ጠቁመዋል።

ትውልዱን በዕውቀት ብዛት መሳል ብቻ ሳይሆን በትምህርት የተላለፍነው በጎነትን፣ ቅንነትን እና ስብዕናን በሚያጎላ መንገድ እየተቀረጸ መሆኑን የትምህርት ተቋሞቻችን ሊፈትሹ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

አዲሱ ዓመትም የሰላም፣ የበረከት በብዙ መልኩ የምንናፍቀው እረፍት የምናገኝበት፣ አገራችን ዜጎቿ በሰላም፣ በወንድማማችነት፣ በመግባባት እና በአንድነት የሚኖሩባት አገር እንድትሆን ምኞታቸውን ገልጸዋል።



ፎቶ ዳኜ አበራ

ሼህ አብዱልሰመድ አሊ

## ኪታብ አጫርተው ለጥምር ጦሩ ድጋፍ ያደረጉት

ጌትነት ተስፋማርያም

ሼህ አብዱልሰመድ አሊ በደቡብ ወሎ ዞን ከለላ ወረዳ የሚገኘው የሰላም መስጂድ ኡስታዝ ናቸው። ጥምር ጦሩን በምን አይነት መንገድ እንደሚደግፉ ሲያሰላስሉ ቤታቸው ውስጥ የተቀመጡ ኪታቦች አሊያም የሃይማኖት መጻሕፍትን መጠቀም እንደሚችሉ ማሰባቸውን ያስታውሳሉ።

ኢማሙ የያዙትን ሃሳብ ወደተግባር ለመቀየር አላመነቱም። በሚያስተምሩበት መስጂድ ውስጥ ህዝበ ሙስሊሙን ካሰባሰቡ በኋላ ብዙ ዓመታት ያስተማሩባቸውን ኪታቦች እንዲገዟቸው ለጨረታ አቀረቡ።

ተማሪዎቻቸውንም ከኪታቡ ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ለጥምር ጦሩ ድጋፍ እንደሚውል አስረድተው በአስተባባሪነት ከመደቡ በኋላ ጨረታውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቁ።

መምህሩ ለጨረታ ካቀረቧቸው ኪታቦች ከ13 ሺህ ብር በላይ በማግኘታቸው ፤ ድጋፉን ይዘው ግንባር ለሚገኘው ጥምር ጦር ማስረከባቸውን ተናግረዋል።

አንድነታችንን ሊበታትን የመጣውን ወራሪ ለመመከት ግንባር ላይ ላለው ጥምር ጦር በአቅሜ ድጋፍ በማድረግ አብሮነቴን አሳይቻለሁ ያሉት ሼህ አብዱልሰመድ ፤ በራያ ቆቦ ግንባር ለተሰለፈው ጥምር ጦር ድጋፍ ሲያደርጉ አገኘናቸው።

በወቅቱ ሼህ አብዱልሰመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቡድኑ ወረራ በሚፈጽምባቸው አካባቢዎች ቁርዓንን አቃጥሏል መስጅድና የሐይማኖት ስፍራዎችንም አፍርሷል።

ቡድኑ ለጥፋት የተፈጠረ መሆኑንም በተደጋጋሚ ጊዜ አሳይቷል፤ ሃይማኖታችንም ደግሞ እንደሚያዘው ቁርዓንን ያቃጠለን ሰውን ሊደድል የመጣውን ተዋጋው ይላል።

እኔ ደግሞ የሃይማኖት አስተማሪ ነኝ፤ ወደግንባር ሄጄ እንዳልተኩስ የክላሽ አጠቃቀምም ችሎታው የለኝም። በገንዘብ እንዳልደግፍ ደግሞ ሀብትም የለኝም። ነገር ግን የማስተምርባቸውን መጻሕፍት ለጨረታ በማቅረብ ጥምር ጦሩን መደገፍ በመቻሌ ደስተኛ ነኝ ብለዋል።

በወቅቱ አስራ አራት ጥራዝ ያለው ተፍሲር ነበረኝ እሱውን ለጨረታ አቅርቤያለሁ ያሉት ኢማሙ፤ ስራዬን ያየ ሰው ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ተረባርቧል። ጨረታው ሲካሄድ ተበድሮ ጭምር ድጋፍ ስታደርግ ጨምርበት ብሎ ገንዘብ የሰጠም አለ። ሕዝቡም ለሠራዊቱ በሚደረገው ድጋፍ ትልቅ መነሳሳት ታይቶበታል ሲሉ ተናግረዋል።

ሃይማኖትና ብሔር የማይለየውን አጥፊ ቡድን ለመመከት ግንባር ላይ ለሚገኘው ጥምር ጦር በቀጣይም አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ አገራችን ጸንታ የምትቆመው በልጆቿ አጥንትና ደም መሆኑ ይታወቃል። አሁንም በግንባር መስዋዕትነት ለሚከፍሉ የሠራዊት አባላት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ወጣቱም በበኩሉ በየመንገዱ ዳር ከሚነዙ አሉባልታዎችና ከማህበራዊ ሚዲያ የሐሰት መረጃዎች በመራቅ የየአካባቢው ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ መጠናከር አለበት። ወራሪው ቡድን ቤተሰቦቹን ሊገድል፣ ንብረቱንም ሊዘርፍና ሴቶች ላይም ጥቃት ሊያደርስ መምጣቱን በመገንዘብ ከጦሩ ጎን መሰለፍ አለበት ብለዋል።

ሼህ አብዱልሰመድ እንዳስታወቁት፤ ሰላምን ለማስፈን ከአሉባልታና አላስፈላጊ ወሬዎች በመውጣት በአንድነት መቆም ይገባል። ብሔርና ሃይማኖት ሳይለይ አንድነታችንን ለመፈረካከስ የመጣውን ወራሪ የሕወሓት ቡድን በምችለው አቅም ሁሉ መዋጋት ያስፈልጋል።

# ቤትን ምሉዕ ያደረጉ የበጎነት ስራዎች

ዘላለም ግዛው

‹‹ቤቴ የፈራረሰ፣ ግድግዳው ያዘመመ፣ በዝናብ ወቅት መዘፍዘፊያ ተደቅኖ የምኖርበት ነበር፡፡አሁን በበጎ ፈቃደኛ ባለሀብትና በመንግሥት አካላት ታድሶልኝ በማየቴ ደስታዬን የምገልጽበት ቃላት የለኝም›› ይላሉ ሾላ ገበያ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 በተለምዶ ታቦት ማደሪያ አካባቢ ነዋሪዋ ወይዘሮ አሚና ፈረጃ፡፡

ወይዘሮ አሚናን ያገኘናቸው የአዲስ አበባ ከተማ የትላልቅ ግንባታ ፕሮጀክት ግንባታ ጽህፈት ቤት ከልማት ዘርፍ አካላቱ ጋር በጋራ በስድስት ክፍለ ከተሞች ያከናወናቸውን የአቅመ ደካማ ቤቶች እድሳት አጠናቆ ባስረከበበት ሥነሥርዓት ላይ ነው፡፡

ወይዘሮ አሚና ‹‹ጉልበት በከዳኝ፣ ሕመምም በተጫነኝ ወቅት እንዲህ አይነት ድጋፍ ማግኘት ደስ ያሰኛል›› የሚሉት ወይዘሮ አሚና፤ በእድሳቱ ሃሳብ ከማመንጨት ጀምሮ የተሳተፉ ሁሉ ፈጣሪ ቤተሰቦቻቸውን እንዲባርክላቸውም ይመርቃሉ፡፡

አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የደስታ የአንድነት ይሁን። ለተቸገሩ ሁሉ ፈጣሪ ለእኔ እንደደረሰ ይድረስላቸውም ይላሉ፡፡

በመርሃ ግብሩ ግንባታውን ያከናወነው የቲኤንቲ ስራ ተቋራጭ ተወካይ አቶ ኪዳኔ ንጉሴ የነበረውን ቤት በማፍረስ ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር በፈጀ ወጪ ለኑሮ ምቹ የሆነ ቤት በመገንባት ለነዋሪዎቹ መተላለፉን አንስተዋል፡፡

በችግር ውስጥ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ማገዝ አስፈላጊ ነው፡፡እያንዳንዱ ሰው የቻለውን በማድረግ ቢተባበር ችግረኞችን መደገፍ ያስችላልም ነው ያሉት፡፡

አልጋ፣ ቡፌ፣ የሶፋ መቀመጫ በማሟላት፣ ወለል በማልበስና አስፈላጊ ግብአት በማሟላት ርክክብ ተካሂዷል፡ ፡በዓሉንም በተበረከተላቸው ሙክት በግ አሳልፈዋል፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በሪሁን አዳነ፤ በወረዳው ዘንድሮ 42 የችግረኛ ቤቶች ተገንብተው መተላለፋቸውን ያስታውሳሉ፡፡በተለየ ሁኔታ የቲኤንቲ ስራ ተቋራጭ እንደግል ቤቱ ተጠናቅቆ ገንብቶ አስፈላጊ ግብአቶችን በማሟላት ስላስረከበልን ምስጋና ይገባዋል ነው ያሉት፡፡



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

ለኑሮ የማይመች፣ በላስቲክ የተጠጋገነ እና ግድግዳው በድጋፍ የቆመ እንደነበር በመጥቀስም፤ ከአሁኑ ገጽታ ጋር ሳነጻጽረው በጎነትና ቤት ማደስ ማለትን በሚገባ ይረዳዋል። በጎነት ከልብ ሲሆን ቤት በምሉእነት ይሰራል ይላሉ አቶ በሪሁን፡፡

የአዲስ አበባ የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ደቦ ቱንካ (ኢንጂነር)፤ ችግረኞችን በበጎነት በመደገፍ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ጽህፈት ቤቱ በተመረጡ ቦታዎች ሰርቶ እያስረከበ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

ጽህፈት ቤቱ ግዙፍ የሆኑ ከተማዊና አገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶችን ከማስገንባት ጎን ለጎን በዚህ አይነት የበጎ ተግባር ላይ በመሰማራት ዘንድሮ ከ30 ቤቶች በላይ ግንባታቸውን እያካሄድን እንገኛለን ሲሉም አስረድተዋል፡፡

በአዲሱ ዓመት በዘመናዊ ቤት ውስጥ ከነሙሉ እቃቸው እንዲያሳልፉ መደረጉ ትልቅ እመርታና ሁሉም ሰው ሊማርበት የሚገባ ነው፡፡በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚኖሩ የከተማው ነዋሪዎች ለበዓል የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በመለገስ የበጎነትን እርካታን እንዲያገኙ ተደርጓል፤ ተግባሩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ነው የጠቆሙት፡፡

አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የብልጽግና፣ የአንድነት እንዲሁም የእድገት እንዲሆንም መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ቤት ለታደሰላቸው ነዋሪዎችም ከመልካም ጤንነት ጋር በቤታቸው እንዲኖሩም ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

የየካ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሞገስ አባተ በበኩላቸው፤ ጽህፈት ቤቱ ከዋና ተግባሩ ጎን ለጎን በችግር ውስጥ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መመልከቱ ይበል ያሰኛል ይላሉ፡፡በሚያስተባብራቸው ድርጅቶቹ አማካኝነት እንዲደገፉ፣ እንዲታገዙ እና ኑሯቸው እንዲሻሻል እየተሰራ ያለው ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

በችግር ውስጥ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መርዳት ከምንም በላይ ያስደስታል፡፡ችግረኞችን የመደገፍ ተግባሩን ሌሎቹም ሊከተሉት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ዜና

# ምስጢራዊ ሰነዱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ያየው ገነት ገለጹ ።

ረዳት ፕሮፌሰር ያየው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰሞኑን ሾልኮ በወጣው የትህነግ ምስጢራዊ ሰነድ ቡድኑ የተሰራበትን ማንነት አጋልጧል፤ ለትግራይ ሕዝብ ጥቅም እንዳልቆመም አሳይቷል ።

ሰነዱ በትግራይ ያለው ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጦርነት ካላገኛቸው ከሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከሚታየው አንጻር የተሻለ ማለቱ በራሱ ቡድኑ በሕዝብ ስም ለመነገድ ወደኋላ የማይል መሆኑንና ለሕዝብ ደንታ እንደሌለው ያሳያል፤ በአንጻሩ ቡድኑ ራሱ ቀደም ሲል በአካባቢው ችግር እንዳለና እርዳታ እንዲገባ ሲጮህ እንደነበረ ይታወሳል ብለዋል ።

አሸባሪ ቡድኑ በከፈተው ጦርነት ምክንያት መሰረተ ልማት እንዲቋረጥና ለተቸገሩ የአካባቢው ነዋሪዎች ሰብአዊ ድጋፍ እንዳይደርስ ምክንያት ከሆነ በኋላ በግልጽ የሚታየውን የትግራይን ሕዝብ ችግር መካዱ የቡድኑን አረመኔያዊነት በግልጽ አሳይቷል ።

ረዳት ፕሮፌሰር ያየው፤ ትህነግ ለትግራይ ሕዝብ የሚጨነቅ አለመሆኑን በሰነዱ መመላከቱን አንስተዋል ።ባለፉት ዓመታት ከውጭ ሃይሎች ጋር በርእዮተዓለም እውነተኛ የሚባል ልዩነት እንዳልነበረው፣ ከውጭ ጠላቶች ጋር በማበር የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ ሲሰጥ መቆየቱንም አመልክተዋል ።

በኅሬላ ጦርነት ወቅትም ቡድኑን ሲያስታጥቁት፣ በተለያዩ ድጋፎች ሲታገዝ የነበረው በውጭ ሃይሎች እንደነበር በማስታወስም፤ እንዲያድኑትም እንደሚፈልግ፣ እነርሱም ወደማእከላዊ መንግሥቱ እንዲመለስ እንደሚፈልጉም አመልክተዋል ።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ጦርነቱ እልባት አግኝቶ በኢትዮጵያም ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን በኢትዮጵያ በኩል የተወሰደውን የሰላም አማራጭ ትህነግ ሊቀበል ይገባል። ለትግራይ ሕዝብም የሚሻለው አማራጭ ይህ ነው ።

የሸብር ቡድኑ ቅድመ ሁኔታ የሚያቀምጠው ድርድሩን ለማደናቀፍ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ያየው፤ በሕወሓት በኩል የሚነሱ ነጥቦች በድርድር ጊዜ እንጂ በቅድመ ድርድር ጊዜ የሚነሱ እንዳልሆኑ አመልክተዋል ።ለሕዝቡ ሰብአዊ ርዳታ የሚደርስበትን መንገድም ማመቻቸት እንዳለበት አሳስበዋል ።

ቡድኑ አፍሪካዊ መፍትሄን በመግፋት በውጭ ሃይሎች መፍትሄ ማመኑ የተሰራበትን ማንነት ያሳያል፣ ሥልጣን ላይ እያለም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም በማሳለፍ ለውጭ ሃይሎች የሚጋለብ ፈረስ እንደነበረም አመልክተዋል ።

ቡድኑ አፍሪካዊ መፍትሄን አለመቀበሉ፤ ለአፍሪካ ሕብረት ያለውን ንቀት የሚያሳይ፣ አፍሪካዊ ተቋማትን በማዳከም የውጭ ሃይሎች ፍላጎትን የማሳካት ሕልሙን የሚያንጸባርቅ መሆኑንም ነው የጠቆሙት ።

ትህነግ በድርድር ወቅት በሰጥቶ መቀበል አያምንም።ለአፍሪካዊ ተቋማት ካለው ንቀት የተነሳም የአፍሪካ ሕብረትን በመግፋት በውጭ ሃይሎች አደራዳሪነት እንዲካሄድ ይፈልጋል ።ቡድኑ የውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነትን የሚፈልገው ለእርሱ ጥቅም ብቻ እንደሚቆሙ ስለሚያውቅ ነው ።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ያላትን ተደማጭነትም ሆነ ጉልህ ታሪክ አይፈልጉም፣ አያምኑበትም ። በሕብረቱ አደራዳሪነት ችግሩ እንዲፈታም አይፈልጉም ።በዚህ የተነሳ በወያኔ አማካኝነት ይህንን ታሪክ ለማጥፋት ይሰራሉ ብለዋል።

ቡድኑ የተሰራበት ማንነት ከትግራይ ሕዝብ ጋር የሚገናኝ አይደለም ።ለሕዝብ ጥቅም ቢያስብ ኖሮ ለአፍሪካውያን ጥቅም ሊሆን የሚችለው አፍሪካዊ መፍትሄ መሆኑን ይገነዘብ ነበር እንጂ በምእራባውያን ጣልቃ ገብነት የሚደረገው ድርድር መፍትሄ አይደለም ሲሉም ተናግረዋል ።

ሕወሓት አህጉራዊ ተቋማትን ማጥላላቱ የአፍሪካ ተቋማት እንዳይጠነከሩ በውጭ የሚደረጉ ጫናዎች ማሳያ ነው ።‹‹አፍሪካ ለዓለም ሥልጣኔ ምንም አላበረከተችም›› የሚሉ የውጭ አገራት ምሁራንን በመከተል ንቀትን አሳይቷል ።ነገር ግን የመጨረሻ ምርጫችን የሚሆነው እና መፍትሄ የምናገኝበት በአፍሪካዊ መፍትሄ ነው።

ሩዋንዳውያን ለከፍተኛ ብጥብጥ ሲዳረጉ፣ ያንን ያህል የዘር ጭፍጨፋ ሲካሄድ የውጭ ሃይሎች መፍትሄ አላመጡም ።ሶማሌ ውስጥ ያለው ችግርም ምዕራባውያን ሊፈቱት አልቻሉም ።ሶማሌ ላይ ያለው ችግር መሻሻል ያሳየው በአፍሪካዊ መፍትሄ ነው ።በመሆኑም አፍሪካዊ ተቋማትን ልንቀበል፣ ችግራችንን እንደሚፈታ ልናምን ይገባል ብለዋል ።

ሰሞኑን ከሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ሾልኮ የወጣው ሰነድ እንዳጋለጠው ሕወሓት የራሱን ሥልጣን እስካስጠበቀለት ድረስ ከአሸባሪው አልሸባብ ጋር ጭምር ለመስራት የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው ።ከዚህም አልፎ ለትግራይ ሕዝብ የሄደለትን የርዳታ ምግብ ለጦርነት ለማዋል መጋዘኖችን እስከመቆጣጠርና መዝረፍ መሄዱም ይታወሳል።

# አሸባሪው ሕወሓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደገለጹት፤ በዚህ ሳምንት ከቡድኑ ማዕከላዊ ኪሚቴ ሾልኮ የወጣ ሚስጥራዊ ሰነድ "የሰብአዊ እርዳታን ትግላችንን ለማጠናከር እንጠቀማለን፤ በትግራይ ያለው የኢኮኖሚ ችግር የተጋነነ ነው" ማለቱ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ አጠናክሮ መቀጠሉን ያሳያል።

እንደ አቶ ሃይለ ገለጻ፣ ቡድኑ ለሰብአዊ እርዳታ የገባውን ነዳጅ በግልጽ መዝረፉና የትግራይን ችግር መካዱ ፤ ለትግራይ ሕዝብ ክብር እንደሌለው እና ለሥልጣኑ ብቻ እንደሚያስብ ያሳያል።

ቡድኑ እርዳታውን በሚስጥርም ሆነ በግልፅ ለራሱ ዓላማ ሲጠቀምበት ቆይቷል ያሉት አቶ ሃይለ፤ እንዲህ አይነት ሃሳቦች አሁን በግልጽ በሰነዱ ውስጥ ማስፈሩ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም ብቻ እየታገለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ሲሉ ገልጸዋል ።

አቶ ሃይለ እንዳሉት፤ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ እርዳታ አቅራቢዎችን በቁጥጥራችን ስር እናደርጋለን ማለቱ የሚያስገርም አይደለም ።ይህ ሲጠቀምበት የቆየው አካሄዱ ነው፤ በግልጽ ነዳጅ ዘርፈዋል፤ ይህ ተግባር የትግራይን ሕዝብ በረሃብ እንዲያልቅ እየሰራ እንደሆነ እና ዓለም ዓቀፍ ወንጀልም ጭምር ነው ብለዋል።

ይህ ቡድን የትግራይን ሕዝብ ሰላም፣ ልማት፣ ዴሞክራሲና ፍትህ እንዳያገኝ እየሰራ ነው። ወደ ሕዝብ የሚመጣውን ሰብአዊ እርዳታ እቆጣጠራለሁ ማለት የሽፍታ ባህሪ ነው፤ ከተራ ሽፍታነት የዘለለ ከፍተኛ ኢሰብአዊ ድርጊትም ነው ብለዋል።

በትግራይ ያለው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከሌሎች ክልሎች ሲነጻጸር ብዙም አይለይም ማለቱ ትክክል አይደለም። አካባቢው በጦርነት የተጎሳቆለ ነው፤ የችግሩን መጠን ዓለም ያውቀዋል፤ ለዛ ነው እርዳታ እንዲገባ የተፈቀደው፤ ህክምና እና ምግብ የሌለው ክልል ጦርነት ካልተካሄዳቸው ሌሎች ክልሎች የተሻለ ነው ማለት በሕዝቡ ላይ ማፌዝ ነው ብለዋል።

ቡድኑ ይህንን የተናገረው በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ስቃይ ስለማያስጨንቀው እና ጉዳዩ ስላልሆነ ነው ሲሉም አብራርተዋል።

በተመሳሳይ ሰላምን ውድቅ ያደረገው የትግራይን ሕዝብ ችግር ውስጥ በማስገባት እራሱን በሥልጣን ላይ ለማቆየት ስለሚፈልግ ነው ያሉት አቶ ሃይለ፤ የትግራይ ሕዝብ በችግር ውስጥ መኖሩን እያወቀ ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን በሰነዱ እራሱን ማጋለጡ በትግራይ ሕዝብ ላይ ምን ያህል ንቀት እንዳለው የሚያመላክት ነው ብለዋል።

# “ኢትዮጵያ በልጆቿ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መወያየት እና የጋራ ግንዛቤ መያዝ አስፈላጊ መሆኑንም ገልጸዋል።

በመድረኩ በብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት በኩል በሰላምና ደህንነት ላይ የቀረበው የውጭ እና የውስጥ የደህንነት ስጋቶችን በተለይ የውስጥ የደህንነት ስጋታችን የሚመነጨው በአብዛኛው ከፖለቲካ ጥያቄ፣ ከኢኮኖሚ ጥያቄ፣ እና ከዚህ ውስጥ ከሚመጩ የዴሞክራሲ፣ የብሔር፣ የሃይማኖት ጽንፈኝነት እና ሌሎች ስጋቶች ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑ የተመላከተበት ነው ብለዋል።

ዶክተር ይልቃል እንደገለጹት በውጭ እስካሁን ጫና ሆነው ኢትዮጵያን እያሰቃዩ ከሚገኙ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኞቹ የዓባይ ግድብ እና ከዛ ጋር የተያያዙ የልማት ፕሮጀክቶች ናቸው። ከዚያም በላይ አብዛኛው ድንበራችን ያልተካለሉ በመሆናቸው የውዝግብ እና የውጭ የደህንነት ስጋት የሚፈጥር መሆኑ በተግባር እየተፈተንበት ነው ብለዋል።

ከለውጡ በኋላ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት ተቋምን ሪፎርም ለማድረግ፣ አገሪቱ ያሉባትን የደህንነት ስጋቶች ለማስወገድ መረጃዎችን በአግባቡ መሰብሰብ፣ ማጠናከርና ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ በማቅረብ የኢትዮጵያ ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ከገጠማትም በድል የሚቋጭበት መንገድ የተሰራበት መሆኑን አድንቀዋል።

በለውጡ ተቋሙን ሕዝባዊ በማድረግ ሂደት ሕዝቡ ተቋሙ የኔ ነው በሚል እምነት የተቻለውን ተሳትፎ እንዲያደርግ የተደረገው ጥረት በሌሎች አገሮችም የብሔራዊ መረጃና ደህንነት የሚሰበስበውን፣ የሚያሰራጨውን መረጃ የማግኘት እና የመግዛት ፍላጎት እያሳዩ ናቸው ብለዋል።

ተቋሙ እየተለወጠ መሆኑን እና ይህን ለማድረግም የሰው ኃይልን የተማረ፣ ሙያዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ለማድረግ የተሰሩ ስራዎችም ምን ያህል ወሳኝ እንደሆኑ ጠቁመዋል።

መከላከያ ሠራዊታችን በዚህ ወቅት በጀግንነት እየተፋለመ ሲሆን የአገራችን አንድነት፣ የሕዝባችንን ህልውና ለማረጋገጥ ታላቁን ሕይወት እየሰጠ ይገኛል። የሀገር ትልቁ መለያ ሉዓላዊነት ነው። አገር የማይደፈር፣ የማይገረሰስ መብት አለው። የዚህ ሉዓላዊነት መገለጫ እና ማስጠበቂያ ዋናው ተቋም መከላከያ ሠራዊት ነው ሰሉም ተናግረዋል።

ከለውጡ በኋላም መከላከያን ከብሔር ተኮር የአመራር እና የሠራዊት ስብጥር አውጥቶ ወደ ህብረብሔራዊ እና ሀገራዊ ተቋም ለማድረግ የተሰራውን ለውጥ አድንቀዋል።

የመከላከያ የጥንካሬ ሚስጢር የአገራችንን አንድነት እያጠናከረ፣ ጋሻ እና መከታ እየሆነ በውጭና በውስጥ የሚነሱ የሉዓላዊነት ጸር የሆኑ ኃይሎችን የሚመታ ኃይል መሆኑ ነው። አሁንም አገር ለማፍረስ የተነሳውን ወራሪ ቡድን ከሕዝቡ ጋር በመሆን እየመከተ ነው ብለዋል።

የመድረኩ ዓላማ “ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች” ነው ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ በየዘመኑ በርካታ ሉዓላዊነቷን፣ አንድነቷን የሚገዳደሩ የውስጥ እና የውጭ ኃይሎችን በአንድነት ተባብረው እየመከቱ እና ሰንኮፉን እያመከኑ አሁን ካለንበት ደረጃ ደርሰናል። ወደ ፊትም እንቀጥላለን። ከዚህ አንጻር ወቅቱን በሚመጥን ደረጃ የቀረበው ፓናል ውይይት ሰላም ለሀገር መሰረታዊ እሴት ነው። ይህን እሴት መገንባት፣ መንከባከብ አለብን ብለዋል።

ሰላም የብልጽግና እና የመረጋጋት ጎዳና በመሆኑ ይህን ለማደፍረስ ጋሬጣ የሆኑ አካሎች ካሉ ደግሞ የፖሊስ ተቋም ወንጀልን በመከላከል ሙያዊ፣ ቴክኒካዊ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም በማጣራት አስፈላጊ ከሆነም እርምጃ በመውሰድ በተለይ ሉዓላዊነትን የሚያጠቃ የሚደፍር ካለ ደግሞ መከላከያ ኃይላችን ያለበትን ቁመና እየገነቡ መሄዱ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የፓናል ውይይቱ መረጃ ለሰላም፣ ለፖሊስ ለመከላከያ ሰራዊት ተቋሞች አስፈላጊ በመሆኑ ለአገራችን ሰላም እና ደህንነት በትብብር እና በቅንጅት መስራት እንደሚገባ የተመላከተበት ነው ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ የእነዚህ ድምር ውጤት ከሌሎች ያልተጠቀሱ አካላት ጋር በመሆን ኢትዮጵያ እያሸነፈች እንድትሻገር የሚያደርጉ ተቋሞች መሆናቸውን አስገንዝበዋል።

# የምርኮኞቹ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መካከል እማሆይ ማይጠምቱ ገብረ እግዚአብሄር አንደኛዋ ናቸው ። እማሆይ ማይጠምቱ የ 75 ዓመት መነኩሲት ሲሆኑ እንደማንኛውም መነኩሴ የፀሎት ማድረሻ መቁጠሪያ አድርገዋል ፤ የምንኩስና ኮፍያ ደፍተዋል ።

በዚህ እድሜአቸው ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ለኢትዮጵያ እና ሕዝቧ ደህንነት ፀሎት ማድረግ ነበረባቸው ።ይሁን እንጂ የሸብር ቡድኑ እማሆይ ማይጠምቱን በማስገደድ መቁጠሪያ ይዘው ፀሎት በሚያደርጉበት እጃቸው ቦምብ አሸከማቸው ።ዓለም በቃኝ ያሉትን መነኩሴ ለእኩይ ተግባሩ ማስፈጸሚያ አዋላቸው ።

እንደ እማሆይ ማይጠምቱ ገለጻ ፤ አሁን ላይ ለጥምር ጦሩ እጃቸውን በመስጠታቸው ሕይወታቸውን ከማትረፋቸውም ባለፈ ለበርካታ ወራት እህል እርቆት የነበረውን አፋቸውን ከእህል ማገናኘት ችለዋል ።

የእርዳታ እህል በየጊዜው መጣ ሲባል እንደሚሰሙ የተናገሩት እማሆይ ማይጠምቱ ገብረ እግዚአብሄር፤ አንድም ቀን ግን የእርዳታ እህል ደርሷቸው እንደማያውቁ ይናጋራሉ ።

ሌላኛው የሸብር ቡድኑ ቦምብ አሸክሞ የላካቸው የ72 ዓመቱ አዛውንት አቶ ተክለሃይማኖት ተስፋየ ናቸው ። አቶ ተክለሃይማኖት ተስፋየ ከእድሜያቸው መግፋት በተጨማሪ አይነ ስውርም ናቸው ።ይሁን እንጂ በጭካኔው ወደር የማይገኝለት የሸብር ቡድኑ አዛውንቱን አይነ ስውር በሕጻናት እያስመራ ቦምብ አሲዞ ወደ ግንባር ላካቸው ።አቶ ተክለሃይማኖት እንኳን ቦንብ የሚወረውሩበት አቅም ሊኖራቸው ይቅርና በቅጡ መራመድ አይችሉም ። ይህ ግን ለሸብር ቡድኑ ምኑም አይደለም ።

ለትግራይ ሕዝብ የስንዴ እርዳታ መጣ ሲባል ቢሰሙም አንድም ቀን እርዳታ አግኝተው እንደማያውቁ አቶ ተክለሃይማኖት ይናገራሉ ። እህልን ጠግበው ከበሉ በርካታ ወራቶችም ተቆጥረዋል።ለዚህ ምስክር አያሻም ፤ የደረት አጥንታቸው ፈጦ እና ገጦ ይመሰክራል ።

ልጆቻቸውን ለውትድርና ከሰጡ የስንዴ እርዳታ እንደማይሰጣቸው ተነግሯቸው እንደነበር ያስታወሱት አቶ ተክለሃይማኖት ፤ ይሁን እንጂ ለአቅመ አዳም የደረሱትም ሆነ ሕጻናት ልጆቻቸውን ለውትድርና ቢሰጡም እስካሁን ምንም አይነት እርዳታ እንዳልተሰጣቸው ይገልጻሉ ።

የሸብር ቡድኑ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን አረመኔያዊ ተግባር ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ተባብረው እንዲያስቆሙ ጥሪ አቅርበዋል ። በውጭ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ሕወሓት እየፈጸመ ያለውን አረመኔአዊ ተግባር በጥብቅ እንዲያወግዙ ጥሪ አቅርበዋል ።

ሌላኛው በወያኔ ተገዶ ወደ ውትድርና እንደገባ የሚናገረው ምርኮኛ ደግሞ ግርማይ ለገሰ ይባላል ።ግርማይ የሶስት ልጆች አባት መሆኑን እና ካልዘመተ የእርዳታ ስንዴ እንዳመይሰጠው በሸብር ቡድኑ እንደተነገረው ይገልጻል ። በዚህም ሶስት ልጆቹ እና ባለቤቱ በርሃብ ከሚያልቁ ራሱ በጥይት ሙቶ ቤተሰቡን ለመመገብ ወስኖ የሸብር ቡድኑን ሠራዊት ተቀላቀለ ።አርሚ 17 በሚባል ወታደራዊ ቡድን ውስጥ ተመድቦ ለጦርነት ወደ ግንባር መጣ ።ነገር ግን የሕወሓትን ተልዕኮ ሳያምንበት በመግባቱ በውጊያ ላይ እጅ መስጠቱን ይናገራል ።

ከተወሰኑ ወራት በፊት ለቤተሰቡ ከሶስት ወር አንዴ ብቻ የእርዳታ እህል ይሰጣቸው እንደነበር መስማቱን የተናገረው አቶ ግርማይ ፤ አሁን ላይ ግን ቤተሰቦቹ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ እንደማያውቅ ገልጿል ።

ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሎም መላው የዓለም ሕዝብ ሊያወግዘው እንደሚገባም ጥሪ አቅርቧል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሸብር ጥፋትና ሴራ የአሸባሪው ሕወሓት የዕድሜ ዘመን ባህሪ ነው!

አሸባሪው ሕወሓት እንደ ፍጥረቱ ክፉና ሴረኛ መሆኑን አጠናክሮ ቀጥሎበታል፤ ራሱ በከፈታቸው ሁለት ጦርነቶች ድል ተደርጎና አያሌ የትግራይ ልጆችን ለጦርነት ማገዶም ሶስተኛውን ጦርነት ከፍቷል።ይህን ጦርነት የከፈተውም መንግሥት ደጋግሞ ለሰላም የዘረጋለትን እጅ ገፍቶ ነው።በእጅጉ ሲዘጋጅበት የቆየው ጦርነትም በጥምር ጦሩ በአስተማማኝ ሁኔታ እየተመከተ ይገኛል።

መንግሥት ለዘላቂ ሰላም ለዕድገትና ብልጽግና መሰረቱ ሰላማዊ አማራጭ መሆኑን ገልጾ አስፈላጊውን ዝግጅት ሲያደርግ ቢቆይም፣ ቡድኑ ግን በተጠናወተው የጦርነት አባዜው ቀጥሎበታል።ጦርነት መክፈት ልማዱ የሆነው ይህ ቡድን ሶስተኛውን ዙር ጦርነት በሀገር ላይ ከፍቷል፤ ሰሞኑን አፈትልኮ በወጣው ሚስጥራዊ መረጃውም በኃይል ወይም በጦርነት ሥልጣን የመያዝ አቋሙን ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል።

ይህ መረጃ ቡድኑ ከስህተቱ ጨርሶ የማይማር ይልቁኑም ቀውስ መደገስ የተጠናወተው መሆኑን በሚገባ አጋልጧል።በኃይል ሥልጣን ለመያዝ ሲያደርግ የቆየውን ጥረት አሁንም አጠናክሮ የሚቀጥልበት መሆኑን መረጃው አጋልጧል።የፌዴራል መንግሥት ለሰላም ያቀረበለትን እጅ ገፍቶ «ሁለንተናዊ ላለው የመጨረሻው ምዕራፍ ዘመቻ ልንዘጋጅ ተገደናል» ሲልም የሽብር ዕቅዱን በሰነዱ ላይ በግልጽ አስታውቋል፡፡

ቡድኑ ለሰላም ፊቱንም ቢሆን ቁርጠኛ እንዳልሆነ ይታወቃል፤ ይልቁኑ የሁል ጊዜም ምኞቱና የማይጨበጠው ህልሙ የመንግሥትነትን ሥልጣን በኃይል በሴራና በሽብር መቆናጠጥ ነው ።ለዚህም ነው በመንግሥት ላይ ጫና ለማሳደር በሚል በመላ ኢትዮጵያ ግጭቶችን እያስነሳ ንጹኃንን በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲጨፈጨፉ እያደረገ ያለው።እንደማያዋጣው እያወቀም ቢሆን ለሶስት ጊዜ ጦርነቶችን በተደጋጋሚ መክፈቱም ይህ ኃይል ጸረሰላምና ቆሞ ቀር መሆኑን ያመላክታል።

ሰላምን በጦርነት ማምጣት እንደማይቻል ከከፈታቸው ጦርነቶች ሊማር አልፈለገም።ሰላም እንቅልፍ ስለሚነሳውና ሕዝብ ከተረጋጋ የሚጠይቀውን ጥያቄ መመለስ ስለማይችል ህልምና ዕቅዱ ሁሉ ጦርነትና ጦርነት ብቻ ነው።በአጠቃላይ የተፈጠረው፣ የኖረውና የሚኖረውም በጦርነት ብቻ እንደሆነ አድርጎ የሚያስብ ቡድን ነው።

በተለያዩ ጫናዎች የተነሳ ስለሰላም ቢናገር እንኳ ለይስሙላ ነው። ለዚህም አንዱ ማሳያ የሚሆነው «በጦርነት ሂደት ውስጥ የመረጃ ልዕልና ለማግኘት እና በርካታ ኃይሎችን ከጎንህ ለማሰለፍ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች አንዱ፣ ለዓለም አቀፉ ማሕብረሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ቁርጠኝነት እንዳለህ አስመስለህ ራስህን ማቅረብ መሆኑ ሊረሳ አይገባም።» ሲል ሰሞኑን አፈትልኮ በወጣው መረጃው ላይ ያሰፈረው ሃሳብ ነው።ቡድኑ ፊቱንም ቢሆን ለሰላም ቁርጠኛ ሳይሆን ለይስሙላ ሲንቀሳቀስ እንደነበር ከዚህ መረጃም መረዳት ይቻላል። የዘላቂ ሰላም ዋስትና የሚረጋገጠው በሰላማዊ አማራጭ ሳይሆን በክንዳችን ብቻ ነው ብሎም በሰነዱ ላይ አስፍሯል፡፡

ቡድኑ የሽብር ጥቃቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ነው በሰነዱ የተመለከተው።ለዚህም «ሽብር፣ ፍርሃትና የሥነ ልቦና ጫና መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ ሽብር የሚያስፋፉ እና በመሀል ሀገር ያለው ሕዝብ ሳይቀር በመንግሥት አቅም ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር የሚያደርጉ መረጃዎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች በሙሉ ማዳረስ ያስፈልጋል" ሲል ሀገር ለማፍረስ ምን ያህል እንደሚሄድ በግልጽ አመላክቷል።

አሸባሪው ሕወሓት አጋሬ የሚላቸውንና ራሱ ጠፍጥፎ የሰራቸውን እንደ ሸኔ ያሉትን አሸባሪዎች እና ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶችን ለሀገር ማፍረስ ዓላማው ለመጠቀም ማቀዱንም ገልጿል።ቡድኑ በሰነዱ የሸኔ ቡድን በመንግሥት ክፉኛ እየተመታ መሆኑን ገልጾ፣ ወደ አዲስ አበባ በሚያደርገው የመጨረሻ የትግል ምዕራፍ ላይ ሸኔዎች የቅርብ አጋዦች እንደሚሆኑ አስታውቋል።

ቡድኑ ይህ ብቻ አልበቃውም፤ በሶማሌ ክልል አካባቢ በክልሉ ከሚንቀሳቀሱ እንደ አልሸባብ እና የኦጋዴን ታጋዮች ጋር የመረጃ ልውውጥ፣ እገዛ እና ስትራቴጂያዊ ሥራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አስታውቋል። የሽብር ቡድኑ በዚህ ብቻ ሳይገደብ በዓለምአቀፍ ደረጃ በአሸባሪነት ተፈርጆ በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ፣ በሶማሊያ፣ በኬንያ ጭምር እርምጃ እየተወሰደበት ያለውንና አጋሩ አርጎ የያዘውን አልሸባብን ሳይቀር ሥልጣን ላይ ለመቆናጠጥ ለማደርገው ጥረት አጋሬ ነው ሲል አስቀምጧል።

ከላይ የተገለጹት እውነታዎች ቡድኑ በቀቢጸ ተስፋ ውስጥ ሆኖም አሁንም ዋነኛ ዓላማው ለብዝበዛና ዘረፋ ሥልጣን መያዝ መሆኑን ያመለክታሉ።

ቡድኑ ሥልጣን ላይ ለመውጣት አጋሮቹ በሚላቸው እንደ ሸኔ ባሉት ተላላኪዎቹ እንደ እስከ አሁኑ ሁሉ አሁንም በንጹኃን ደም ለመነገድ በመስራ ላይ መሆኑም ግልጽ ሆኗል።በዓለምአቀፍ ደረጃ በአሸባሪነት የተፈረጀውን አልሸባብን ጭምር እንደ እስከ አሁኑ ሁሉ ለእዚህ ተግባሩም ለማሰለፍ አቅዷል።እነዚህ ቡድኖች ንጹኃንን በአሰቃቂ ሁኔታ በመጨፍጨፍ ይታወቃሉ፤ ይህ ግፋቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ነው የቡድኑ ፍላጎት።

ሸኔና አልሸባብ በመከላከያና በየክልል ልዩ ኃይሎች ክፉኛ እየተመቱ መሆናቸውን ቡድኑ እያወቀም ለሽብር ስትራቴጂው አጋር አድርጎ ማስቀመጡ ሽብር ጥፋትና ሴራ የአሸባሪው ሕወሓት የዕድሜ ዘመን ባህሪ መሆናቸውን በሚገባ ያረጋገጠ ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ካለፈው ጦርነት ብዙ ልንማረው የሚገባ ...

**በምስጋና ፍቅሩ**

ባለፈው ዓመት በሀገራችን በሰሜኑ ክልል በተደረገው ጦርነት የውጭም ይሁን የሀገር ውስጥ ጣላቶቻችን ስንገዳገድ የወደቅን መስሏቸው ደስታቸው ከአቅም በላይ ሆኖ ነበር። ይሁን እንጂ ያሰቡት እንዳላሰቡት፤ የገመቱት ፣ እንዳልገመቱት ፤ የጠበቁት እንዳልጠበቁት ሆኗል። በዚህም የተፈጠረባቸው ግራ መጋባት የወቅቱ ትልቁ አጀንዳ እንደነበር ለማስታወስ ሩቅ አይደለም።

ይህ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ መንግሥት ለሰላም እድል ለመስጠት በሚል እጆቹን ለሰላም በማንሳት የተናጠል የተኩስ አቁም አውጆ ፤ ሀገርን ከጥይት ድምጽ ፤ትውልድን ከእልቂት ፤ የሀገር በረከቶችን ከጥፋት ለመታደግ ሰፊ መንገድ ተጉዟል። በዚህ ለጊዜውም ቢሆን ሀገራዊ እፎይታ ተፈጥሯል።

ይህ የመንግሥት የሰላም መንገድ ገና ከጅምሩ ያልጠዋጠለት አሸባሪው ሕወሓት ፤የተለያዩ አደናቃፊ ሃሳቦችን በመኮልኮል ለሰላም ምንም አይነት እድል መስጠት እንደማይፈልግ በተጨባጭ አሳይቷል። ከዚህም አልፎ እንደለመደው ግጭቶችን በመፍጠር ሀገርና ሕዝብን ወደ አላስፈላጊ ጦርነት ጎትቶ አስገብቷል።

አሁን ጦርነት ለሶስተኛ ጊዜ በአዲስ መልክ ተጀምሯል፤ ዛሬም ድረስ ስለሰላም የሚጮሁ ብዙ ድምጾች ቢኖሩም ፤ በቡድኑ በኩል አድማጭ አላገኙም። ከዛ ይልቅ ዓለም አቀፉን ሕብረተሰብ ግራ በማጋባት ከጦርነት የማትረፍ የውልደት ባህሪውን በአደባባይ ሲገልጽ እየታየ ነው።

ቀደም ባለው ጦርነት ሕጻናት እና ሴቶችን ጨምሮ ራሳቸውን ከዓለም አግልለው ለፈጣሪ ለመገዛት የመነኮሱት ጭምር ተጠቂ ሆነዋል። ሕጻናት ያለአሳዳጊ ቀርተዋል፤ አረጋውያኑም ያለጠዋሪ ቀርተው የሞቀው ጎጇቸው እንዲቀዘቅዝ ምክንያት ሆኗል። ክቡር የሆነው የሠው ልጅ ሕይወት እንዳልሆነ ሆኖ አልፏል።

ከሰው አልፎ ተርፎና ለሠው ልጆች ምግብነት የሚውሉ እንስሳት በቁማቸው በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ ሆኗል። በጦርነቱ ምን ያልተፈጠረ ነገር አለ? ብዙዎች ካደጉበት፤ ንብረት ካፈሩበት ወግ ማረጋቸውን ካዩበት (አይበታለው ብለው ተስፋ ካደረጉበት ) ቀያቸው ተፈናቅለው የሠው እጅ ጠባቂ ሆነዋል።

የነገ ትውልድ ማፍሪያ ይሆናሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው ትምህርት ቤቶችም ግማሾቹ ሙሉ በሙሉ ሲወድሙ ሌሎቹ ደግሞ በከፊል ውድመት ደርሶባቸዋል። ተማሪዎችም ቢሆን ከትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳይገኙ ከማድረግ በሻገርም ለሥነ ልቦና ጉዳት ተዳርገዋል። ሰዎች ሲታመሙ፣ ነፍሰጡሮች ምጥ ሲገጥማቸው በፍጥነት የሚያቀኑባቸው ሆስፒታሎች እንዳልሆኑ ሆነው እነርሱም ዳግም መታከምን እና መታደስን ፈልገዋል። ከጦርነቱ ባልተናነሰ መንገድ አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴ ምርት በመደበቅ፤ ዋጋ በማናር ማሕበራዊ ምስቅልቅል እንዲፈጠር ረጅም መንገድ ተጉዘዋል። በዚህም በደሃው ሕዝብ ላይ ምሬትን በመፍጠር በመንግሥት ላይ ጫናዎችን ለማበራከት ሰርተዋል። በለውጡ ተስፈኛ የነበረውን ሕዝብ ከተስፋው ለመነጠል የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

ጦርነቱ በተካሄደባቸው አካባቢ ጉዳት የደረሰባቸውን ተቋማትም ይሁን መሠረተ ልማቶችን ለመገንባት ብዙ ዓመታትን ሊፈጅ እንደሚችል ይታመናል ፤ ይህም ሀገሪቱም ማደግ ያለባትን ወይም መድረስ ያለባት የእድገት ደረጃ ላይ እንዳትደርስ ሳንካ መሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም ።

ጦርነት ሊያደርስ ከሚችለው ቁሳዊ፣ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራዎችን አንጻር ዛሬም ሰለሰላም የተሰጠውን እድል መጠቀም ተገቢ ነው ። በተለይም አሸባሪው ሕወሓት ከለመደው የጥፋት፤ የግርግርና የማጭበርበር መንገድ ወጥቶ ለሰላም እድል ሊሰጥ ይገባል።

የሀሰተኛ መረጃዎችም ጉዳይ ከሰላም ጥረቱ ጋር ታሳቢ ሊደረግ የሚገባ ነው። ባለፈው የጦርነት ወቅት ሀገራዊ ፈተና ከነበሩት መካከል ሀሰተኛ የመረጃ ስርጭት እንደነበር የሚታወስ ነው ፤ ይህም ለጦርነቱ አቅም ሆኖ የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን ለማሰብ የሚከብድ አይሆንም።

የሀሰተኛ መረጃዎች ምክንያት ብዙዎች ተረብሸው፤ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንኳን ግራ ተጋብተው አስተውለናል። ዛሬም ቢሆን ሀገሪቱን ለማተራመስ በማሰብ የሽብር ወሬ የሚነዙ በርካታ መሆናቸውን በማሰብ ችግሩን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። መንግሥትም መረጃዎች ማጥራት እና በፍጥነት ለሕብረተሰቡ ማድረስ ይጠበቅበታል።

ባለፈው ጦርነት የውጭ ጣልቃ ገብነት እስከምን እንደነበር የሚረሳ አይደለም። አንዳንድ ሀገራት ጦርነቱን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመምራት እና ኢትዮጵያን በእጅ አዙር በባርነት ለመቀራመት ፍላጎት ማሳየታቸውንም በወቅቱ የታዘብነው ነው። ይህንን እውነታም በጥንቃቄ ማየቱ ተገቢ ነው።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ጉዳይ እኛ ኢትዮጵያውያን ዛሬም ለመደጋገፍ እና ለመረዳዳት ወደ ኋላ የማንል ሕዝቦች መሆናችን ካሳዩ ክስተቶች አንዱ ያለፈው ጦርነት ነበር። ጦርነቱ በሌለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያውያም በጦርነቱ ቀጠና ያሉ ንጹሐን ዜጎችን ለመደገፍ የሄዱበትን መንገድና ቁርጠኝነት ዛሬ ላይ ልንደግመው ይገባል።

በጦርነት ቀጠና ለሚገኙ ወገኖቻችን ዛሬም ለእለት ጉርስ የሚሆናቸውን ምግቦች ፣ አልባሳት፣ ለሴት እህቶቻችን የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን እና መሰል ድጋፎችን በአይነትም ይሁን በጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅብናል። የወደሙ ተቋማትን ለመጠገን እና ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ለማድረግ ግለሰቦች፣ማሕበራት፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ያሳዩትን ድጋፍና ርብርቦሽ ሊደግሙት ያስፈልጋል።

የሃይማኖት ተቋማት ተሰሚነታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ ሲቪክ ማሕበራት፣ አክቲቪስቶች ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች በሁሉም መንገድ ሕዝባችን ከትናንቱ ጦርነት ተምሮ፤ ስለ ሰላምና ለሰላም ልቡን እንዲሰጥ ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

ጦርነትን በጦር ሜዳ ማሸነፍ በራሱ አልፋና ኦሜጋ አይደለም ፤አልፋና ኦሜጋ የሚሆነው በሰላም ማሸነፍ ሲቻል ነው። ተስማምቶ ፣ ተፋቅሮ፣ ጥላቻን እና ቂምን ትቶ፣ ይቅር ተባብሎ ሁለንዋ ለሠላም መዘርጋት ሲቻል ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የፋሽን መልክ በአዲስ ዘመን

ተገኝ ብሩ

### ዘመን በራሱ ሲፈሽን

ኢትዮጵያውያን አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር ይዋባሉ። ታዲያ ውበታቸው በተፈጥሮም ይደምቃል። ምድር በአዲስ ዓመት ትዋባለች። በአዲስ ዓመት ኢትዮጵያ ላይ ሰው ብቻ ሳይሆን ዘመን በራሱ ይፈሽናል። ወቅቱ በራሱ አዲስነት ይላበሳል። ሜዳና ጋራው አረንጓዴ ለብሶ፣ የለመለመ መስኩ በአደይ አበባ ደምቆ ልዩ ውበት ይላበሳል። ልክ እንደ ፋሽን ወቅቱም የውበት ሰገነት ይለብሳል። በዚህ ጊዜ ክረምት ያደመነው ሰማይ ይጠራል፤ በጎርፍ የደፈረሰው ውሃ ፀድቶ ኩልል እያለ ይወርዳል።

ሰዎች በዚህ ወቅት አዲስ መንፈስ ይላበሳሉ። በአዲስ ዓመት የአዲስ መንፈስን ለመላበስ ዘመን ባፈራው አልባስ አጊጠው፤ ጊዜው በፈጠረው የውበት ማድመቂያ ተውበው ከዘመድ አዝማድ ጋር ይገናኛሉ። የኢትዮጵያውያን የጥበብ ባለሙያዎች እጅ ያረፈባቸው አልባሳት ማጌጫ፤ ለበዓሉም ልዩ ድምቀት ይሆናቸዋል። ዲዛይነሮች የሰሩዋቸው አዳዲስ ማራኪ አላባሳት የፍስሀ ቅባቸው ማድመቂያ ያደርጉታል። አገሬውም ይህን አስመልክቶ ዘመኑን በራሱ መንገድ ይቀበላል።

### አዲስ ዘመን በልጃገረዶች

በአዳዲስ ልብስ ተውበው፣ፀጉራቸውን ሹሩባ ተሰርተው፣ ከሌላ ጊዜ በተለይ ሹሩባ የተሰሩት ፀጉራቸው ላይ አደይ አበባ ወይም አደይ አበባን በሚመስል ቀለምና ቅርፅ የተሰራ የፀጉር ማጌጫ ደምቀው በየቤቱ እየዞሩ በውብ ዜማ የአዲሱን ዓመት ብስራት ያጋራሉ።

ቀደም ብለው ሕፃናት የራሳቸውን አልባሳት አጥበው ወይም ደግሞ የተገዛላቸው ልብስ ለብሰውና አጊጠው አባበአየወሽን ያሳልፉት ነበር። ዛሬ ላይ አዲስ ነገር ተለምዷል። ተመሳሳይ የሆነ ዲዛይን ያለው የአገር ባህል ልብስ አሰፍተው መልበስ ተለምደዋል። በተለይ አሁን ላይ እየተለመደ የመጣው የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች አልባሳት

**በእርግጥ ከሌሳው ዓውዳመት የሚለዩበት የአለባበስ ሥርዓት ወይም ልምድ ባይኖርም አሁን ላይ የተለያዩ የአገር ባህል አልባሳት ተውበውና በተለያዩ ዲዛይኖች አምረው በዓሉን ያሳልፋሉ**

ተጎናፅፈው አዳዲስ የዲዛይን ለውጦች የተደረገባቸው ባህላዊ ልብሶች ለብሰው የዘመን መለወጫውን ጥዑም ዜማ እያንቆረቆሩ በየቤቱ ይዞራሉ። አሁን ላይ ልጃገረዶች በእጃቸው አደይ አበባ ይዘውና የተለያዩ የአዲስ ዓመት መልካም ምኞት መግለጫ ካርዶችም ይዘው መዞር ጀምረዋል።

### አዲስ ዘመን በወንድ ልጆች

በእርግጥ ከሌላው ዓውዳመት የሚለዩበት የአለባበስ ሥርዓት ወይም ልምድ ባይኖርም አሁን ላይ የተለያዩ የአገር ባህል አልባሳት ተውበውና በተለያዩ ዲዛይኖች አምረው በዓሉን ያሳልፋሉ። ሙሉ ነጭ በነጭ የሀበሻ አልባሳት ከታች ሱሪና ከላይ በሚያማምሩ ዲዛይኖች የተሰሩ የሸሚዝ ቅርጥ አልያም የክናቴራ መልክ ያለው የባህል አልባሳት በሕፃናቱ የሚዘወተር ነው።

በእርግጥ ከለበሱት የዓውዳመት ልብስ ጋር በመልክና በዲዛይን የሚመሳሰሉ ጫማዎች በሕፃናቱ አልፎ አልፎ የሚዘወተር ነው። የተለየ የጫማ አለባበስ ሥርዓት በሕፃናቱ አይታይም። ከአልባሳት ባለፈ የሚጫሙት ጫማ ለበዓሉ በተለየ መልኩ በፋሽንነት የሚጠለቅ ሳይሆን መደበኛ ወይም በአዘቦት ጊዜ የሚደረጉ የጫማ አይነቶች ይደረጋሉ። ወንድ ሕፃናት ከዚህ ቀደም ባሉት ዓመታት እንደሚያደርጉት ሁሉ፤ አበባ ስለውና በየዘመድ አዝማዱ ቤት አልያም ጎረቤት የሚዞሩበትና አበባውን የሚሰጡበት ነው አዲስ ዓመት።

### አዲስ ዘመን በወጣቶች

ዛሬ ላይ ትውልዱ ለአገሩ ባህል ትኩረት የሰጠ ይመስላል። በተለይ በበዓል ወቅት ይሄ ይገለጣል። ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እንደቀደመው ጊዜ የተዘጋጁ የውጭ ሀገር ልብሶች በበዓል ሰዓት አይለብሱም። የአገር ባህል አልባሳት በተለያየ መልክና በሚፈልጉት ዲዛይን አሰርተው መልበስ ልምዳቸው አድርገዋል። ለአዲስ ዓመትም ይህንኑ ባህላዊ አልባሳት በተለያየ ዲዛይን አሰርተው ይለብሳሉ።

ይበልጥ በሕፃናት ወጣቶች አልባሳትና ዜማ የሚደምቀው አዲሱ ዓመት ለአዋቂዎችም እንደ መስኩ ሁሉ የራሱን አዲስ ውበት ያላብሳል። ዛሬ ላይ ለባህሉ ልዩ ትኩረት የሰጠ ትውልድ ተፈጥሯልና ባህላዊ አልባሳት በብዙዎች ይዘወተራሉ።

ዛሬ ላይ ሀበሻ ልብስ ዋንኛ መታያ ጊዜው የበዓል ወቅት በተለይም እንዲህ ሰማይ ምድሩ በሚፈካበት አዲስ ዓመት ነው። ሀበሻዊ አልባሳት የሚነግሱበት በዓል ነውና የሀገር ባህል አልባሳት ከተሞቻችን ያጥለቀልቃሉ። የአገር ባህል አልባሳቱን የተጎናፀፉ ሰዎች መንገዶች ሞልተው ይታያሉ። ተጣጥፎ ከተቀመጠበት ሳጥን ተሸጉጦ ከከረመበት ቅርጫት ወጥቶ ታጥቦና ተተኩሶ ከሰው ጋር ይቀላቀሉበታል።

ኢትዮጵያውያን የራሳችን የሆነ ከሌሎች የሚለየን በራሳችን ጥበብ ተቃኝቶ ከአኗኗር ዘይቤያችን ተቀድቶ ተጎናጸፍነው የሚያምርብን ጥበብ ተላብሰነው የምንደምቅበት የባህል ልብሳችን መለያችን ነው። በተለይ እንዲህ በበዓል ወቅት እምር ብለን የምንታይባቸው የባህል ልብሶቻችን ባህሎቻችንን ያንፀባርቁልናል።

ሀበሻ ጠቢብ አይደል በራሱ ሸማ አዲሱን ዓመት በጥበበኞቹ በተሰሩ አልባሳት ይደምቃል። ቀድሞ የነበረውን የተለመደ የባህል አልባሳት ዛሬ ላይ በበዙት ዲዛይነሮቻችን ከሁሉ ጋር በልክ የተሰፋ ያህል ልዩ ውበት እንዲላበስ ማድረግ ችለውበታል። የፋሽን ዲዛይነሮች ዘመኑ የሰጣቸውን እውቀትን ተጠቅመው ቀድመው በልምድ ያገኙትን ከህሎቱ ጋር አዋዶ ጥበብ ላይ ጥበቡን ድርቦ ለልብስነት ያበቃዋል። አገሬው ደሞ ከራሱ ጋር የሚሄደውን መርጦ አዲሱን ዓመት አዲስ ሆኖ ይቀበልበታል።

እንዲህ አውዳመት በተለይ ሰማይ ምድሩ በሚፈካበት አዲስ ዘመን ላይ የባህል አልባሳት በማህበረሰቡ መዘውተሩ የላቀ ጠቀሜታ አለው። አጋጣሚው አገራዊ አልባሳት ወደገበያው በዝተው እንዲቀርቡ በማድረግ የኢኮኖሚና የባህል እድገቱ ላይ ታላቅ አዎንታዊ ሚና በመጫወትም ላይ ይገኛል። በሙያው ዘርፍ ያሉ ተዋንያንም ተጠቃሚና በብዙ መልኩ እራሳቸው የመለወጥ እድሉን ያሰፋላቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ለራሱ ባህል ልዩ ትኩረት እንዲሰጥና ለአገራዊ ምርቶች የተሻለ ቦታ እንዲኖረው ያደርጋል። በዚህም እንደ አገር ይህ በጎ ልማድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ሊያስገኝ መቻሉ እሙን ነው።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## እቅዳችን

አቤል ገ/ኪዳን

አዲስ ዓመት መጣ። እንደተለመደውም በአዲስ መልክ አዲስ ተስፋ ልንሰንቅ ተዘጋጅተናል። መቼም የሰው ልጅን የሚያኖረው ተስፋ ነውና ተስፋ ማድረግ መልካም ነው። አንዳንዶች ደግሞ ከተስፋም አልፈው እቅድ ማቀድ ሁሉ ከጀመሩ ሰንብተዋል። እሱም መልካም ነው። ማቀድ የመሰልጠን ምልክት ነው። በጨበጣ ከመወዛወዝ ማቀድ የተሻለ ነው። ስለዚህም የዛሬው ጉዳያችን በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

የመጀመሪያው ጉዳይ ማቀድ አሪፍ ነገር ሆኖ ሳለ ለማቀድ ብቻ ስለሚያቅዱ ሰዎች እንነጋገር። አንዳንድ ሰው የሚያቅደው ለማቀድ ያህል ነው። በቃ አለ አይደል የሆነ በሕይወቱ ላይ ቀልድ የማያውቅ ቆፍጣና ሰው ለመመምሰል። ከዚያ ውጭ ለምን እንዳቀዱ፤ ምን እንዳቀዱ ፤ እንዴት እንደሚያሳኩት ምናምን አያውቁትም። ተገድደው ያቀዱት ነው የሚመስሉት። እቅዳቸውን አያውቁትም ፤ አይፈልጉትም፤ አያምኑበትም፤ ሊያሳኩት አይተጉም፤ ግን ያቅዳሉ። እንደዚህ አይነት ሰዎች ከአንዳንድ የመንግሥት ተቋማት ጋር ይመሳሰላሉ።

ከዚያ ደግሞ አሉ የተለጠጠ እቅድ በማቀድ ራሳቸውን የሚያጽናኑ። ከአቅማቸው በላይ የሆነ እቅድ ያቅዳሉ። ለምሳሌ ገና የሴት ጓደኛ እንኳ ሳይኖራቸው በዚህ ዓመት ትዳር እይዛለሁ ብለው የሚያቅዱ ፤ ፓስፖርት ሳይኖራቸው ከሀገር እወጣለሁ ብለው የሚያቅዱ ፤ የባንክ ደብተራቸው ገና ባለ አራት አሀዝ ቁጥር እያሳየ ቤት እና መኪና እገዛለሁ ምናምን የሚሉ። የአብዛኞቹ እቅድ ከማለት ይልቅ ወደ ምኞት የተቃረበ ነው። አትኩረን ብናያቸው ብዙዎቹ አነቃቂ ንግግር አብዝተው የሚሰሙ እና የንግግሩ ሞቅታ አልለቅ ያላቸው ናቸው። አነቃቂ ንግግር መስማት መጥፎ ባይሆንም ወደ እቅድ ሲገባ ግን ንግግሩ እቅድ ተደርጎ አይጻፍም። መሬት ላይ የወረደ እና የሚጨበጥ ነገር ማቀድ ያስፈልጋል።

ቀጥሎ ደግሞ በጣም ደካማ እቅድ የማቀድ ልምድ ያላቸው ሰዎችን እናያለን። እነዚህ ደግሞ የሚያቅዱት የአዘቦት ውላቸውን ነው። መድከም አይፈልጉም። መታገል አይፈልጉም። እንዲሳካላቸው ግን ይመኛሉ። ስለዚህ የሆነች እቅድ ቢጤ ያቅዳሉ። ከዛ እቅዷን ቅልብጭ ያለች ናት ብለው ያደንቋታል። አትኩረን ስናየው ግን እቅዱ የሰነፍ እቅድ እንደሆነ እናያለን። ምንም አዲስ የስኬት አቅጣጫ የሌለው፤ ድካም የማያስከትል፤ የአምናው ምኞታቸው ሌላ ኮፒ ሆኖ ይመጣል። እንዲህ አድርገው የሚያቅዱት በሕይወታቸው ውስጥ የሚታቀድ ነገር ጠፍቶ ሳይሆን እቅዳቸውን ለማሳካት የሚያስፈልገውን ድካም መድከም ስለማይፈልጉ ነው።

ከዚያ ደግሞ አሉልህ አማራጭ የሌለው እቅድ የሚያቅዱ። እንግዲህ ሁላችን እንደምናውቀው ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ ለእቅድ የማይመች ነው። ነገሮች ቶሎ ቶሎ ይቀያየራሉ። አብዛኛው ለውጥ ደግሞ በጎ የሚባለው አይነት አይደለም። ሌላ ሌላውን ትተነው አሳካዋለሁ ብለህ ያቀድከውን እቅድ ለማቀድ መስከረም ላይ ሶስት መቶ ሺ ብር ይዘህ እንደሆነ አንተ እቅዱን ለማስፈጸም ጥር ላይ ስትነሳ ዋጋው ሰባት መቶ ሺ ደርሶ ታገኘዋለሁ። እንዲህ እንዲህ እያልን ብዙ የማይገመቱ ሁኔታዎችን ልንጠቅስ እንችላለን። አንዳንድ ሰዎች ግን ሀገሪቱ እንዲህ የማይገመት ሁኔታ ውስጥ ሆና እንኳ የሚያቅዱት እቅድ አንድ ነገር ላይ ብቻ ሙጭጭ ያለ ነው። ሁኔታዎችን ያላገናዘበ እቅዳቸው ሲከሽፍ ምን አማራጭ እንዳስቀመጡ ስለማያውቁት እጅ ለመስጠት ፈጣን ናቸው።

ከዚያ ደግሞ ጭራሽ እቅድ የሚባል ነገር የሌላቸው ሰዎች አሉ። ምነው ስትላቸው ፈጣሪን ይጠቅሱብሃል። እጣ ፈንታቸው በፈጣሪ እጅ የተጻፈ መሆኑን እና የእነሱ ማቀድ ብዙም ፋይዳ እንደሌለው ይነግሩሀል። ሰው ሲያቅድ ፈጣሪ ፈገግ ይላል ምናምን ይሉህና ማቀድ አላስፈላጊ እንደሆነ ይሰብኩሀል። ፈጣሪ ራሱ የልባችንን መሻት አይቶ አይደል ወይ የሚያግዘን ስትላቸው ሌላ ጥቅስ ያመጡና ክርክሩን ያሰፉታል። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመከራከር የሚያወጡትን ጉልበት እና ጊዜ ለማቀድ ቢያወጡት ይሻላቸው ነበር። ሌሎች ደግሞ የማያቅዱት ልምዱ ስለሌላቸው ነው። በቃ ዝም ብለው ይኖራሉ። በእነሱ ዓለም ውስጥ ከጸሀይ በታች አዲስ ነገር የለም አዲስ ነገር እንዲኖርም አይፈልጉም። የሚፈልጉት ዝም ብሎ መኖር ነው። በጳጉሜን 5 እና በመስከረም 1 መካከል ምን ልዩነት አለ ይሉሀል። ነገሮች በራሳቸው ጊዜ በሕይወታቸው ውስጥ እንዲከሰቱ ይፈልጋሉ እንጂ እነሱ ለዚያ ምንም ጥረት ማድረግ አይፈልጉም።

ለማንኛውም ይህን ሁሉ አየንና ተቸን። ከዚያ መፍትሄው ምን ይሁን ነው ዋናው ጥያቄ። መፍትሄው ከላይ የጠቀስናቸውን ተቃራኒ ማድረግ ነው። በቃ በልካችሁ አቅዱ። ያልተለጠጠ ፤ ስንፍናን የማያበረታ ፤ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ የከተተ፤ እንዲሁ ለማቀድ ሳይሆን ለመፈጸም የሚሆን እቅድ ማቀድ ያስፈልጋል። አላቅድም ማለት አግባብ አይደለም ፤ መብትም አይደለም። አንተ የራስህን እቅድ ካላቀድክ የሌላ ሰው እቅድ አስፈጻሚ ትሆናለህ። ቁጭ ብለህ ነገር እስኪከናወን ከጠበቅክ የሚከናወነው ያንተ ሳይሆን የሌላ ሰው ምኞት ነው። የሚያቅድ ሰው ነገሮች እሱ በሚፈልገው መልኩ እንዲሄዱ ማድረግ ይችላል። የማያቅዱ ሰዎች ግን እንኳን ነገሮችን ለእነሱ ወደሚመች አቅጣጫ ማዞር ቀርቶ እነሱን ብሎ የመጣውን እድልም ያሳልፉታል። ቢያንስ ለእኛ የሚጠቅመንን ነገር እንድናገኝ ጥቂት ነገር እንኳ ማቀድ ይጠቅመናል።

እዚህ ጋር አንድ ነገር ልጨምርና እቅድ ስናቅድ ሁሉን ነገር በእኔ ፤ ለእኔ ተብሎ መታቀድ የለበትም። እድገት የሚመጣው ብዙውን ጊዜ በመተባበር ነው። እኛ በሌሎች ሰዎች እቅድ ውስጥ ቦታ አለን። ሌሎችም በእኛ እቅድ ውስጥ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል። ብዙ እቅዶችም ተሳትፎን የሚጠይቁ ናቸው። ለምሳሌ አገባለሁ የሚል ሰው እጮኛውን የእቅዱ አካል ማድረግ አለበት። ሀብታም እሆናለሁ የሚል ሰው የሀብት መንገዱ በስራም ይገኝ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ ፤ ያኛውን ወገን ታሳቢ ያደረገ እቅድ ማቀድ አለበት። ሰው ማሕበራዊ ፍጡር ነው። ስለዚህም ስኬቱም ሆነ ውድቀቱ ከሌሎች ሰዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን በማወቅ እቅዱ ውስጥ ሌሎችን ታሳቢ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

በመጨረሻም መልእክታችን ፤ እናቅድ ፤ ከማቀድ የሚጎድልብን ነገር የለም። ከዚያ ደግሞ እቅዳችንን ለማሳካት እንሞክር። መሞከር አይጎዳንም። አቅደን ሞክረን ከተሳካልን እሰየው ፤ ካልተሳካልን ደግሞ ያን አጋጣሚ እንደመማሪያ እንጠቀምበት እና ለከርሞው እንሻሻልበታለን። ይሄው ነው።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ኢትዮጵያዊነት በጋራ የጻፍነው የጋራ ታሪካችን ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያውያን በጋራ የጻፉት የጋራ ታሪካቸው ነው። ኢትዮጵያዊነት ለዘመናት ጠብቀንና ተንከባክበን ያዘለቅንው የጋራ ትውፊታችን ነው። ይሄ የጋራ ታሪካችን አሁን ላይ መልኩንና ቀለሙን እያጣ የመጣበት ሰሞን ላይ ነን። ኢትዮጵያዊነት ለምን በዚህ ልክ ዝቅ አለ ብለን ስንጠይቅ የምናገኛቸው ብዙ መልሶች አሉ። ከመልሶቹ መካከል ፖለቲካችንና ፖለቲከኞቻችን የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ።

አሁን ላይ የተፈጠሩ አብዛኞቹ ችግሮቻችን በትናንት የፖለቲካ ሽር ነፍስ የዘሩ ናቸው። የፖለቲከኞቻችን ሃሳብ ምንም ይሁን ማረፊያው ሀገርና ሕዝብ ነው። ሕዝብ ከትናንት እስከዛሬ የፖለቲከኞቻችን ዱላ ገፈት ቀማሽ ነው። ይሄ ችግር እንዲያባራ ሕዝቡም ሆነ ፖለቲከኞቻችን በመተማመን ላይ የተመሰረተ የጋራ ሃሳብ ያስፈልጋቸዋል።

በእርቅና በምክክር ትንሳኤዋን የምታይ ሀገርን ለመፍጠር ሁሉም ዜጋ፣ ሁሉም ፖለቲከኛ ሊተባበር ይገባል። የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በመርህና በእቅድ ደረጃ ለያዘው የለውጥና የስብዕና ግንባታ ተልዕኮ የበኩላችንን በማዋጣት ሀገር በመፍጠር ሂደት ላይ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልጋል።

የብቻ ታሪክ የለንም። ታሪኮቻችንን የፈጠርናቸው በጋራ ሰርተን፣ በጋራ አስበን ነው። ዛሬም የጋራ ታሪክ ለመስራት በጋራ ማሰብና በጋራ መስራት ግድ ይለናል። ፖለቲካው የፈጠራቸው ማሕበራዊ ቀውሶቻችን የሚታከሙት በመነጋገር ብቻ ነው። ልብ ማፍቀር ሲጀምር መጀመሪያ የሚተወው ጥላቻን ነው።

አእምሮ ማሰብ ሲጀምር መጀመሪያ የሚተወው ስሜታዊነትን ነው። በፍቅርና በእውቀት አእምሮና ልባችንን አቀናጅተን ልትፈርስ ያዘመመች ሀገራችንን መገንባት ያስፈልገናል። ማፍቀር ከልክለነው እንጂ ልብ ለማፍቀር ነበር የተፈጠረው..ግን በከበበን ሴይጣናዊ ሃሳብ ልባችንን ፍቅር ከልክለን ጥላቻን አለመድነው።

አእምሮ በጎ ለማሰብ ነበር ህያው የሆነው ግን በከበበን ነውረኛ ድርጊት እኩይ አድርገን ፈጠርነው። እስኪ እንዋደድ.. ያለምክንያት እንድንወድ ነው ሰው የሆነው። ፖለቲከኞቻችን መነጋገር ቢችሉ፣ ችግሮቻችንን በይቅርታ ማለፍ ብንችል ያኔ የሚያቆመን አንዳች ሃይል አይኖርም ነበር።

ኔልሰን ማንዴላ በሮቢን ደሴት ላይ ለሃያ ሰባት ዓመታት ሲታሰር በዙሪያው ያሉ ክፉ ሰዎችን ሁሉ በይቅርታ ነበር ያሸነፋቸው። ከእስር ወጥቶ ያሰቃዩትን ሰዎች አላሳደደም፣ ለበቀል አልተነሳሳም በመተው ማሸነፍን ነው የመረጠው። እኛም ልባችንን ፍቅር፣ አእምሯችንን እውቀት አስተምረን ስለሀገራችን ስንል አንድ መሆንን ነው ማስቀደም የለብን።

ተነጋግሮ ለችግሮቻችን መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ችግሮቻችንን ተንከባክበን ሌላ ችግር እንዲፈጥሩ ማድረግ የሚቀናን ነን። ባጭሩ መቅጨት እየቻልን ግን ደግሞ እሹሩሩ ብለን ያሳደግናቸው ብዙ ችግሮች አሉብን። ዛሬ ላይ አድገውና ጎልምሰው ጣጣ እያመጡብን ያሉት እነዛ ችግሮች ናቸው። ልንዋጋቸው ይገባል።

በጋራ የጻፍናቸውን ኢትዮጵያዊ ታሪኮቻችንን እንዳይንዱብን መፍትሄ ልንሰጣቸው ይገባል። በጋራ ያቆምናቸውን፣ በጋራ የቀለምናቸውን አለለ መልኮቻችንን እንዳያደበዝዙብን ሀይ ልንላቸው ይገባል። በየትኛውም የዓለም ሀገራት ታሪክ ውስጥ ደምቀው የተጻፉ ሕዝባዊ ታሪኮች የአንድነት ታሪኮች ናቸው። ሀገር የሚተሳሰቡ፣ የሚከባበሩ ሕዝቦች ካሏት የሚጻፍ ታሪክ አታጣም።

ሀገር በመነጋገር የሚያምኑ ዜጎች ካሏት ሥልጣኔ አይርቃትም። ታሪክ እውቀትን መሰረት ያደረገ ነው። ሰው በእውቀትም በድንቁርናም ታሪክ መጻፍ ይችላል። የአባቶቻችን ታሪክ በእውቀት የተጻፈ ሲሆን አሁን እኛ እየጻፍን ያለነው ብሄር ተኮር ታሪክ ደግሞ እውቀት የማይጠይቅ የድንቁርና ታሪክ ነው። በእውቀት ከፍ እንበል። በምክንያትና በአመክንዮ እንራመድ። በመነጋገርና በመተማመን ሃይል እናብጅ።

ሀገር መልካም ዜጋ ካላት ሁሌም ታሪክ አላት። ሀገር መልካም ዜጎች ካሏት ሁልም ሰላም አላት። ቤት ሲሰራ የቤቱን ህልውና ከሚያስጠብቁ ግብዓቶች ውስጥ ዋናዎቹ ዋልታና ማገር ናቸው። ቤት ያለ ዋልታና ማገር ዘመን ሊቆጥር አይችልም። ልክ እንደ ቤቱ ሁሉ የሀገርም ህልውና ዜጎቿ ናቸው። ዜጎች እርስ በርስ ካልተከባበሩ፣ እርስ በርስ ካልተባበሩ ሀገር መተማመኛ አይኖራትም።

እንዲህ እንደዛሬው ሰው በዘመን ላይ ሰይጥኖ ታሪክ ከማበላሸቱ በፊት ታሪኮቻችን በጋራ የተጻፉ ነበሩ። እሴቶቻችን ኢትዮጵያዊ ነበሩ። አሁን ሁሉም ነገር ወደ ቡድንና ወደ ግለኝነት ዞሯል። እያባላን ያለውም ይሄ ኢትዮጵያዊነትን የሻረው የእኔነት መንፈስ ነው። መነጋገር አለብን። የጋራ ታሪክ ለመጻፍ ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። የአባቶቻችንን አይነት ታላቋን ዳግማዊ ምድር ለመፍጠር ከዝምታ ወጥተን መነጋገር መቻል አለብን።

ተመልካች ከመሆን ወጥተን እኔም ያገባኛል ስንል ለውይይት በራችንን ክፍት ማድረግ ይጠበቅብናል። መሰረት የሌለው ያልሆነ ወሬ እያወሩ ሕዝብ ከማደናገር የድርሻችንን አንድ እንጨት በማዋጣት ኢትዮጵያን መስራት እንችላለን። ብዙዎች በተገነባ ሀገር እየኖሩ የእኛን ሀገር ለማፍረስ ቀን ከሌት የሚለፉ ናቸው። የእኛን ተለያይቶ መቆም የእኛን መነካከስ የሚፈልጉ እዛም እዚህም አሉ። እኚህን ሀገራት፣ እኚህን ግለሰቦች የምናሸንፈው ለአንድ ዓላማ በአንድ ስንቆም ብቻ ነው።

ወደሚጠቅመን መሄዱ ያዋጣናል። የሚጠቅመን ልዩነታችንን ትተን አንድ ሀገርና አንድ ሕዝብ መፍጠር ነው። የሚጠቅመን ያለ ልዩነት የኖሩትን አባቶቻችንን መምሰል ነው። የሚጠቅመን ከጥላቻና ከመለያየት ወጥቶ ወደሚደነቅ ሀገራዊ ልማት መሄድ ነው። ከማንም በፊት ሕዝብ ነበርን። ከማንም በፊት ሀገር ነበርን። ከማንም በፊት ስልጡን ማሕበረሰብ ነበርን። ከማንም በፊት የሥልጣንና የጀግንነት መሰረቶች ነበርን።

አሁንስ ምንድንነን? ራሳችንን፣ ፖለቲካችንን መፈተሽ ያስፈልጋል። ፍቅር ካለን፣ አንድነት ካለን አሁንም ቢሆን ትልቅ ሀገር መፍጠር እንችላለን። ከዛ በፊት ግን ለራሳችንም ለሌላውም ሰው እንሁን። በሰይፍ ሳይሆን በፍቅር፣ በትግል ሳይሆን በሃሳብ ሌሎችን ማሸነፍ እንልመድ። ውስጣችን የተዘራውን ተዘርቶም የበቀለውን በቅሎም መቶና ስልሳ ያፈራውን እኩይ የጥላቻና የመለያየት የሞት በለስ ነቅለን እንጣል።

ባላየንውና ባልሰማንው ፤በማናውቀውም ታሪክ መባላት ትተን በሰለጠነ አእምሮ ሀገር የሚጠቅሙ የጋራ እውነቶችን እንገንባ..ያኔ ሰው እንባላለን። ያኔ ኢትዮጵያ ታመሰግነናለች። ያኔ ትውልድ ያከብረናል።

የአባቶቻችን ኢትዮጵያ የተገነባችው በአንድነት መሰረት ላይ ነው። የአባቶቻችን ታሪክና ሥልጣኔ ዘመን የተሻገረው በአንድ ዓላማ በቆሙ ልቦች ነው። የእኛም ኢትዮጵያ ከዚህ ውስጥ የምትወጣ ናት። ኢትዮጵያችሁን በንጹህ ልባችሁ በንጹህ ነፍሳችሁ በንጹህ አሳባችሁ ውስጥ እናብቅላት። ይሄ ትውልድ ቀላል አይደለም። በአንድነት ከተነሳ የአባቶቹን እውነት መድገም የሚችል ነው። በአንድነት ከቆመ ዳግማዊ አድዋን የሚፈጥር ነው። ኢትዮጵያን ለመስራት ጊዜው የእኛ ነው።

በግዜአችን ለነገ ዋስትና የሚሆን መልካም ነገር እንስራ እንጂ እንጂ የሚጸጽተንንና የሚያስቆጩንን ነጋዊ ድርጊት በስሜት እንዳንከውን እንጠንቀቅ። ዛሬ ላይ ብዙ ነገራችንን እያጣን ያለንው ትናንት ላይ በሰናቸው ስህተቶቻችን ነው። በዙሪያዬ ያሉ ልክ እንዲሆኑ እኔ ልክ መሆን አለብኝ። የእኔ ልክ ሆኖ መቆም ለአዲሷ ኢትዮጵያ ትልቅ ዋጋ አለው።

የእያንዳንዳችን ወቅታዊ ሁኔታ አዲስ ለምንፈጥረው ሀገርና ሕዝብ የላቀ ዋጋ አለውን ከጥፋትና ከስህተት ርቀን ራሳችንን ልክ በሆነ ቦታ ላይ እናቁም ። ያኔ የሁላችን ኢትዮጵያ በሁላችን ልክነት ውስጥ ትፈጠራለች። ያኔ እንደ አባቶቻችን ትልቅ እንሆናለን። ያኔ የብርሃን ዘመን ይሆንልናል።

**የኢትዮጵያ ቀሚስ የተሰፋው በእኔና በእናተ ባህልና ወግ፣ ልማድና ሥርዓት፣ ቋንቋና ዘዬ ነውና ከዛ ሁሉ ብዙ አይነት መርፌና ክር ውስጥ የራስን ብቻ መፈለግ ኢትዮጵያን ርቃናን ማስቀረት ነውና ልብ ልንል ይገባል። ለኩራት ሲሆን የምንለብሰው፣ ለጥላቻ ሲሆን የምናወልቀው ኢትዮጵያዊነት የለም**

እኛ በባህልና በወግ የታነጹ ርህራሄን ለዓለም ያሳዩ የጋራ እሴቶች ያሉን ሕዝቦች ነን። የትኛውም ዓለም የሚደነቅበት ባህልና ትውፊት ያለን ትውልዶች ነን። ግን በዚህ ሁሉ በረከት ውስጥ የፍቅርን ስፍራ ተንጠራርተን አልደረስንበትም። እየኖርን ያለነው በአባቶቻችን ህቅ ነው። ወጥተን የምንገባው በዚያ ትውልድ ታሪክ ነው። አሁን ላይ የብዙዎቻችን ሩጫ የብቻ ሀገርና የብቻ ታሪክ ለመፍጠር ነው።

መቶ ሃያ ሚሊዮን የሕዝብ ብዛት ባላት ሀገር ላይ፣ ከሰማኒያ በላይ ብሄር ብሄረሰቦች ተሰባጥረው በሚኖሩባት ምድር ላይ በምንም አይነት መልኩ የብቻ ሀገርና የብቻ ታሪክ የማይታሰብ ነው። ኢትዮጵያን የሰሯት ሰማንያና ከዛ በላይ የሆኑ ብሄር ብሄረሰቦች ናቸው። ኢትዮጵያን ያደመቋት የነዛ ብሄር ብሄረሰብ መልክና ቀለም፣ ቋንቋና ዘዬ፣ ባህልና ወግ፣ ስርዐትና ትውፊት ነው።

አሁንም ቢሆን ያለነዛ ብዙ እጆች፣ ያለእነዛ ብዙ ልቦች፣ ያለእነዛ ብዙ ሃሳቦች ኢትዮጵያን ሙሉ አድርገን መስራት አንችልም። ለኢትዮጵያ አሁን ያለነው ሁላችንም እናስፈልጋለን። ኢትዮጵያ መልኳ ፤ ሰማንያና ከዛ በላይ የብሄር ብሄረሰቦችን ቅይጥ መልክ፣ ቅይጥ ታሪክ፣ ቅይጥ ባህል ነው።

ሁላችንም የዚህ ሁሉ ብሄር ብሄረሰብ ቅይጥ መልኮች ነን። ተጋብተን ተዋልደናል። ተዋልደን አንድ ሆነናል። ኦሮሞ ሆነን አማራነት የተጋባብን፣ አማራ ሆነን ኦሮሞነት የተላለፈብን፣ ጉራጌ ሆነን እንደ ትግራዋይ የሆንን፣ ትግሬ ሆነን እንደ ጉራጌ የቆምን፣ ሲዳማ ሆነን ወላይታነት፣ ወላይታ ሆነን ሲዳማነት የተላበስን፣ ጋሞ ሆነን ሌላውን ብሄር የምንመስል ብዙ ነን።

ራሳችንን ብንመረምር በኢትዮጵያ ደግ እጆች ያልታቀፍን፣ በኢትዮጵያ ቅን ልቦች ያልተፈቀርን አንገኝም። ተጠጋግተንና ተነካክተን እስከኖርን ድረስ ሁላችንም አማራም፣ ኦሮሞም፣ ትግሬም ሌላውንም ብሄርብሄረሰብ ነን። ኢትዮጵያዊ ስንባል በዚህ ሁሉ የብሄር ስብጥር ውስጥ አልፈን ነው። ማናችሁ ስንባል ኢትዮጵያዊ ነን ምንለው የክብር ሸማ ባለበሱን ብሄር ብሄረሰቦች ተመጻድቀን ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ በቅለን፣ በዚህ ሁሉ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ሆነን ታዲያ ምናችን ነው የብቻ? የብቻ ኢትዮጵያዊነት የለም።

ከዚህ ሁሉ አንድነት ውስጥ፣ ከዚህ ሁሉ ድብልቅልቅ ውስጥ ራስን ማውጣት ፍጹም የማይቻል ነገር ነው። ከዚህ አንድ አይነት ፈትል ውስጥ፣ ከዚህ የጋራ ታሪክ ውስጥ የራስን አንድ ታሪክ መዞ ማውጣት ኢትዮጵያዊነትን ማጉደል ነው። ከዛ ሁሉ የብሄር ብሄረሰብ ቅይጥ ታሪክ ውስጥ የራስን አንድ ታሪክ ለመምዘዝ መሞከር ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው።

የኢትዮጵያ ቀሚስ የተሰፋው በእኔና በእናተ ባህልና ወግ፣ ልማድና ሥርዓት፣ ቋንቋና ዘዬ ነውና ከዛ ሁሉ ብዙ አይነት መርፌና ክር ውስጥ የራስን ብቻ መፈለግ ኢትዮጵያን ርቃኗን ማስቀረት ነውና ልብ ልንል ይገባል። ለኩራት ሲሆን የምንለብሰው፣ ለጥላቻ ሲሆን የምናወልቀው ኢትዮጵያዊነት የለም። ኢትዮጵያዊነት የትም መቼም ለብሰነው የምንዞረው የኩራት፣ የጽናትና የጀግንነት መንፈስ ነው።

ዛሬ ላይ እንደ ሀገር ግራ የተጋባንው ይሄን የአንድነት ካባ ሲሞቀን እያወለቅን ሲበርደን መደረባችን ነው። በብርዱም በጸሀዩም፣ በክረምቱም በበጋውም ኢትዮጵያዊነት ሁልጊዜም አንድ አይነት ነው። ሲመቸን የምንለው ዜግነት የለም። በችግሯም በደስታዋን ለሀገራችን ታማኝ መሆን አለብን።

ኢትዮጵያዊነት ትርጉም የሚኖረው እንደ አሁኑ ባለው አስቸጋሪ የፈተና ጊዜ ላይ ከጎኗ ስንቆም ነው። በነፈሰበት መንፈስ ሳይሆን ለሀገርና ሕዝብ ህልውና ሲባል ሰላምን፣ አንድነትን ማስቀደም ነው። በሃይል ሳይሆን በጥበብ፣ በአፈሙዝ ሳይሆን በመልካም አንደበት ተነጋግሮ መግባባት ያሻናል። እንዳይፈታ ሆኖ የተገመደውን አንድነታችንን እያሰብን፣ እንዳንለያይ ሆኖ የተሳሰረውን ታሪካችንን እያሰብን መጥፎ ነገሮችን መጸየፍ አለብን። ይሄ ሀገራችንን ከጦርነት ወደ ሰላም፣ ከእኔነት ወደ እኛነት፣ ከብሄር ፖለቲካ ወደ ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ የምንመልስበት ጥበብ ነው።

በአንድ ቀለም፣ በአንድ ሰሌዳ ላይ ኢትዮጵያን መስለው የተሳሉ አንድ አይነት ነፍሶች ልዩነት ፈጥረው ሲገፋፉ እንደማየት የሚያሳዝን ነገር የለም። የጋራ ታሪክ፣ የጋራ ባህል፣ የጋራ እሴት ያለው ሕዝብ በማይመጥነው ትንሽ አጀንዳ አንድነቱን ሲያጣ እንደማየት የሚያሳዝን ነገር የለም።

በሀገር ፍቅር እሳት፣ በሞታቸው ዋልታና ማገር በሆኑ በአባቶች ደምና አጥንት የተገነባች ሀገር በሰላም እጦት መከራዋን ስታይ እንደመስማት ምንም የሚያም የለም። የሀገራችን መጻኢ እድል በእኛ እጅ ውስጥ ነው። ከኋላችን ተፈጥረው ሀገርና ሕዝብ የሆኑ ምዕራባውያንና አውሮፓውያን እንዳያላግጡብን በምክክር የችግሮቻችንን ምንጭ ማድረቅ አለብን።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ተጠቃሚን ተደራሽ እስከ ማድረግ የዘለቀ ቅንጅት

**ስምስም መንግሥቱ**

አረንጓዴ ቀለም ያለውና ከማሽላ ምርት ወይንም ፍሬ ጋር የሚመሳሰል ነው። ለብዙዎችም የተለመደ እንዳልሆነ እገምታለሁ። የምግብ ንጥረ ነገሩ ከፍተኛና ጠቃሚ እንዲሁም በዋጋም ከጤፍ በልጦ በኩንታል እስከ ዘጠኝ ሺ ብር የሚያወጣ መሆኑ የበለጠ ትኩረቴን ሳበው።

ማሾ የሚል መጠሪያ ያለውና ከቅባት እህል ውስጥ እንደሚመደብ የነገሩኝ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ የወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ሕብረት ሥራ ማሕበር ዩኒየን ሥራ አስኪያጅ አቶ ታደሰ ፈቃደ ናቸው፣ ሰብሉ በአማራ ክልል ይፋት ሸዋ ሮቢት አካባቢ እንደሚመረትና አረንጓዴ ወርቅ የሸዋ ማሾ የሚባል ስያሜ እንደተሰጠውም እኚሁ ሃላፊ አጫውተውኛል።

እሳቸው ሰብሉ በሀገር ውስጥ ለምግብነት ከሚውል ይልቅ ለውጭ ገበያ ቀርቦ የውጭ ምንዛሬ ቢያስገኝ ከአምራቹ ባለፈ ለሀገር የኢኮኖሚያዊ እድገት ፋይዳው ከፍተኛ ነው የሚል እምነት አላቸው። የአካባቢው አምራችም ይህንኑ እንደሚመርጥ ነው የተናገሩት። ምርቱ አነስተኛ በመሆኑ ለገበያ የማቅረቡን ምርጫ አስቀደሙ እንጂ፣ በብዛት ተመርቶ ሕዝቡ ለምግብ ፍጆታ ቢጠቀመው ሰብሉ የያዘው ንጥረ ነገር ከፍተኛ መሆኑ በዘርፉ አካላት እንደሚገለጽም ይናገራሉ።

ስለ ማሾ ሰብል ምርትና የአመራረት ዘዴ ከማሕበራዊ ድረገጽ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያስረዳው እንደ ህንድ፣ ቻይና ፓኪስታን፣ ታይላንድ፣ ፊሊፒንስ ባሉ ሀገራት ሰብሉ ይመረታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ፣ እስያ፣ኢትዮጵያና በሌሎችም ሀገሮች መመረት ጀምሯል።

በኢትዮጵያ አዲስ የሆነው ማሾ በአርሶ አደሩ በስፋት ባለመታወቁ ልማቱም ሰፊ አይደለም። ሰብሉ ድርቅን የሚቋቋም በመሆኑ በተለይ ዝናብ አጠር በሆኑ ቆላማ አካባቢዎች ቢመረት ያዋጣል። ምርቱ ከሐምሌ መጀመሪያ እስከ ነሐሴ መጨረሻ ነው የሚከናወነው። የማሾ ሰብልን የማወቅ እድሉን ያገኘሁት የሰሜን ሸዋ የወደራ ሁለገብ የገበሬዎች ሕብረት ሥራ ማሕበር ዩኒየን ‹‹የጋራ ጥረት ለሀገር እድገት›› እንዲሁም ‹‹አምራችነት ለሁለተናዊ እድገት›› በሚል መሪ ቃል ጳጉሜን 2 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰየመው የአምራቾች ቀን በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው ዝግጅት ላይ የአካባቢያቸው የምርት ውጤቶችን ለገበያ ለማስተዋወቅ ይዞ በቀረበበት ወቅት ነው። በዝናብ አጠር አካባቢ ተፈላጊ፣ በምግብነቱም ተመራጭና የውጭ ምንዛሬ በማስገኘትም ባለው የኢኮኖሚ ፋይዳ ስለማሾ ሰብል ብናወሳም፣ ኢትዮጵያ መልካምድሯ ፣የአየርፀባዩዋ፣ ሰፊ መሬቷና የውሃ ሀብቷ ለተለያየ የሰብል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ በመሆኑ በምግብ እህል ራስን ለመቻል የሚደረገውን ጥረት ከማሳካትም ባለፈ የአግሮ ኢንዱስትሪውን (የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ) ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ምርት ማምረት የሚያስችል ዕድል አላት።

በዚህ የአምራቾች ቀን መድረክ ላይ የተገኙት በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፍቅሩ ረጋሳ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ባሳለፈችው አራት የሪፎርም ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የማዕድን ዘርፍ ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የሎጅስቲክ ትራንስፖርት ሥርዓትን ለማሳለጥ፣ በሀገር ውስጥ የምርት አቅርቦትን በመጨመር፣ በውጭ ምንዛሬ በግዥ ወደ ሀገር የሚገቡ የተለያዩ የግብርና ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት እና ወደ ውጭ ለመላክም በብዛትና በጥራት ለመጨመር ሲሰራ ቆይቷል። ለእዚህም በበጋ የቆላ መስኖ ስንዴ ልማት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በቡና ልማት የተመዘገቡት ውጤቶች ማሳያ ናቸው።

በጳጉሜን ሁለት በተሰየመው የአምራቾች ቀን አምራቾች ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁና ለገበያ እንዲያውሉ የማድረጉ ዓላማም በአምራቾችና በመንግሥት የጋራ ጥረት እየተመዘገቡ ባሉ ለውጦች ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር ለ2015 በጀት ዓመት ለበለጠ ውጤት ለመዘጋጀት መሆኑን ጠቁመዋል።

‹‹መስኖ ለምግብ ሉዓላዊነት›› በሚል መሪ ቃል የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርም እየሰራ መሆኑን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ኢ.ንጅነር አይሻ መሐመድ በመድረኩ ላይ ተናግረዋል። ሀገር እንደ ሀገር መቆም የምትችለው ሉዓላዊነቷ ሲጠበቅ ነው። ሉዓላዊነት የሚረጋገጠው በትግል ወይንም ወታደር በማቆም ብቻ ሳይሆን በምግብ እህል ራስን ለመቻል ሲሰራን ነው ያሉት ሚኒስትሯ፣ በዓለም ላይ ያለውን ጫና መወጣት የሚቻለውም አምራች እና በምግብ ሉዓላዊ መሆን ሲቻል መሆኑን አስገንዝበዋል።

> **የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ምሶሶ የሆነውንና ሰፊ የሰው ኃይል በመያዝም ድርሻ ያለውን የግብርና ሥራ በመስኖ መደገፍ ግዴታ የሆነበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። መስኖ ለልማት እንዲውል የመስኖ መሠረተ ልማት በብዛት እንዲከናወን መንግሥት ጥረት አድርጓል። በ2013-2014 የምርት ዘመን የግብርናው ዘርፍ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆን የመስኖ አገልግሎት ጥቅም ላይ መዋል አስተዋጽኦ አድርጓል። ለእዚህም የቆላና የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ይጠቀሳል።**

ወደፊት ጦርነቱ በመሣሪያ ብቻ እንደማይሆን ከወዲሁ አመላካች ነገሮች ይታያሉ ያሉት ሚኒስትሯ፣ በዩክሬንና በሩሲያ መካከል በተፈጠረ ጦርነት ምክንያት ለዓለም የስንዴ ምርት አቅራቢ የሆነችው ዩክሬይን የገጠማትን ፈተናም ጠቅሰዋል። ሀገሪቱ በገጠማት ጦርነት ምክንያት ስንዴ በግዥ ከሀገሪቱ የሚገዙ ሀገሮች ምን ያህል እንደተጎዱም ተናግረዋል። ስንዴን በግዥ የሚጠቀሙ ሀገራት በራሳቸው አምርተው መጠቀም ካልቻሉ ወደፊት የሚሆነው የዓለም ጦርነት የምግብ እንደሚሆን ስጋታቸውን ገልጸዋል።

ስጋቶችን ለመቀነስ ልማትን ማፋጠን ይገባል ያሉት ሚኒስትሯ፣ ለልማቱ ሥራ ወሳኝ ከሆነው አንዱ መስኖ መሆኑንም ተናግረዋል። እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ እንደ ሀገር በመስኖ ማልማት ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም፣ በሚፈለገው ልክ መጠቀም ግን አልተቻለም። ግብርናው በዝናብ ላይ ጥገኛ ነው።

የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ምሶሶ የሆነውንና ሰፊ የሰው ኃይል በመያዝም ድርሻ ያለውን የግብርና ሥራ በመስኖ መደገፍ ግዴታ የሆነበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። መስኖ ለልማት እንዲውል በብዛት የመስኖ መሠረተ ልማት እንዲከናወን መንግሥት ጥረት አድርጓል።

በ2013-2014 የምርት ዘመን የግብርናው ዘርፍ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆን የመስኖ አገልግሎት ጥቅም ላይ መዋል አስተዋጽኦ አድርጓል። ለእዚህም የቆላና የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ይጠቀሳል። የግብርና ሥራ በመስኖ እንዳይደገፍ ማድረግ በግብርና ምርታማነት ላይም ሆነ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል።

በስንዴ ልማት ራስን ከመቻል ባለፈ ለውጭ ገበያ በማቅረብም የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማግኘት እንደ ሀገር የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚጠበቅበትን ተልዕኮ በላቀ መልኩ ለመወጣት ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት የሚሆን የእርሻ ማሣ በመስኖ እንዲለማ ለማስቻል ዝግጁ መሆኑን ሚኒስትሯ አስታውቀዋል። ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ተልእኮውን እንደሚወጣም ተናግረዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለአምራችነት የሚውለውን ሰፊ የእርሻ መሬትና የውሃ ሀብት የማገናኘት ሥራ የሚሰራ ድልድይ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ይህንንም በተጠናከረ መልኩ ለመሥራት ነው ኃላፊነት የተሰጠው ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ሌላው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተልእኮ የአርብቶ አደር ወይንም የቆላማ አካባቢ ልማት ሲሆን፣ አርብቶ አደርነት አንዱ የኑሮ ዘይቤ ነው። ይህም በተለያዩ የሀገሪቱ ፖሊሲዎች ተቀባይነት ያገኘ ነው። ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረግ በራሱ ግብ እንዳልሆነ ግምት ውስጥ በማስገባትም በፖሊሲ ተቀባይነት እንዲኖረው የተደረገውን የሚያስፈጽም አስፈጻሚ ተቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ሰፊ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት የያዙ በመሆናቸው በአካባቢው የሚገኙትን ሀብቶች አካባቢንም ሀገርንም ተጠቃሚ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር እንደፖሊሲ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እየመራ ይገኛል። በዚህ ረገድም ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ ነው።

በመድረኩ የተገኙት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ጎሎልቻ ‹‹ወደ 115 ሚሊዮን ሕዝብ አለን። ከዚህ ውስጥ ደግሞ 70 በመቶ የሚሆነው አምራች ነው። ካመረትን ደግሞ ሸጠንና ለውጠን ገቢ በማግኘት ተጠቃሚ መሆን እንችላለን። ይሁንና በተፈጥሮ ፀጋ የታደልን ብንሆንም፣ አምራች ኃይል ቢኖረንም ምርታማ አይደለንም፤ ገና ወደምርታማነት ለመግባት ጥረት እያደረግን ነው›› ይላሉ።

እንደ ሀገር ሉዓላዊ ሆኖ መኖር የሚቻለው ማምረት ሲቻል መሆኑንም ጠቅሰው፣ በግብርናው ዘርፍ እርሻውን፣ በኢንዱስትሪውም የግብርና ግብዓቶችን ማቀነባበር እንዲቻል ፣ ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለማምረትና እቅዱንም ለማሳካት መንግሥት ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ይገልጻሉ።

ግብርናውን ከኢንዱስትሪ ጋር በማስተሳሰር የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ትላልቅ የማቀነባበሪያና የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማቶችን በመገንባት መንግሥት ኃላፊነቱን ሲወጣ ቆይቷል ሲሉም ይገልጻሉ።

አበረታች ውጤቶችን በማስቀጠል ከፍተኛ ስኬት ለማስመዝገብ በቅንጅት መንቀሳቀስ እጅግ ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ የኢንዱስትሪዎችን ችግር ለመፍታት፣ ዘላቂ የሆነ ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ለሀገራዊ መዋቅራዊ ሽግግር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› በሚል መሪ ቃል በሀገር አቀፍ ደረጃ ንቅናቄ በመፍጠር ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ጥረት መደረጉን ጠቅሰዋል። ጥረቶቹን በማጠናከር ውጤት ለማስመዝገብ ሁሉም በተናበበ መልኩ የየራሳቸውን ተልዕኮ እንዲወጡ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ስድስት አስፈጻሚ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በቅንጅት መንቀሳቀሳቸውን አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ በውስጥም በውጭም በገጠማት የተለያየ ፈተና ውስጥ ሆና በተከናወኑ የልማት ሥራዎች ከፍተኛ የሚባል ስኬት ማስመዝገቧን የተናገሩት የገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሺዴ፤ እንደ ሀገር በተጀመረው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሰፊ ተግባራት መከናወናቸውን ገልጸዋል። አምራች ዘርፉንም በማጠናከር መዋቅራዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው መካከል ግብርና፣ ማዕድንና አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደሚጠቀሱ አስታውሰዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ ፤ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት መሪ እቅድ ከወጪ ንግድ ስብጥር አኳያ ግብርና በ2012ዓም ከደረሰበት 77 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 36 ነጥብ 4 በመቶ፣ አምራች ኢንዱስትሪ በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 13 ነጥብ 3 በመቶ፣ በ2022 ዓ.ም ወደ 48 ነጥብ 4 በመቶ ፣ የማዕድን ዘርፍ ደግሞ በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 6 ነጥብ 9 በመቶ፣ በ2022 ዓ.ም ወደ 11 በመቶ እንዲያድግ መንግሥት አቅዷል።

ይህን ለማሳካት ሰፊ ጥረት ይጠይቃል። ለዚህም መንግሥት ደጋፊ የሆኑ አስፈጻሚ የሚኒስቴር ተቋማትን እንደ አዲስ በማወቀርና የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በመተግበር ላይ ይገኛል ያሉት ሚኒስትሩ፣ የተሳለጠ አምራች ዘርፍ መገንባትና የተጠናከረ ኢኮኖሚ መፍጠር መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪን የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትስስር በማረጋገጥ የግብርናና የማዕድን ኢንዱስትሪዎች የአምራች ኢንዱስትሪውን ፍላጎት በማከለ መልኩ እንዲያመርቱ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

የዘርፎቹን ትስስር የሚያረጋግጡት የትራንስፖርትና ሎጅስቲክ፣ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ምርቶችን በጥራትና በወቅቱ ወደ ተጠቃሚው እንዲደርሱ የትራንስፖርትና የመንገድ መሠረተ ልማት አቅርቦቶችን የማረጋገጥ ኃላፊነቶችን መወጣት ይኖርባቸዋል ፤ እየተወጡም ይገኛሉ ብለዋል።

ወሳኝ የሆነውን አምራችነት ለማረጋገጥ ግን የሁሉንም የጋራ ጥረት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል። የተቋማት ቅንጅትና አብሮነት አስፈላጊነትን ለማስመስከር የሚያስችለውን እንቅስቃሴና የኢትዮጵያ የአምራች ዘርፍ በምን ደረጃ ላይ እንደሆነ ለማሳየት በአምራችነት ቀን ላይ በቁጥር 50 የሚሆኑ ምርቶች በአንድ ቦታ ለማየት መቻሉን ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስትር ዳግማዊት ሞገስ፣ መስሪያ ቤታቸው ለምርት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ወደ ማምረቻ፣ የተመረተውን ወደ ተጠቃሚው በወቅቱና በጊዜው በተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች በማድረስ በቅንጅት ኃላፊነቱን ሲወጣ መቆየቱን ይጠቅሳሉ። ለአብነትም በወጭ ንግድ (ኤክስፖርት) በግብርናው ዘርፍ ከነበሩት ስኬቶች መካከል ምርቶችን በኮንቴነር በማሸግ እንዲጓጓዝ በማድረግ ጥራቱ የተጠበቀ ምርት ተጠቃሚው ዘንድ እንዲደረስ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰዋል።

በተለይም የቡና ምርት 98 በመቶ በኮንቴነር አሽጎ የማጓጓዝ ሥራ መከናወኑን ጠቅሰው፣ የመርከብ፣ የባቡርና የጭነት ትራንስፖርትን በማቀናጀት፣ የማዳበሪያ ግብዓትም በወቅቱ እንዲደረስ፣ ነጻ የንግድ ቀጠና በማቋቋም አምራች የኢንዱስትሪ ዘርፉን ተደራሽ በመሆን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጥረት ማድረጉን ይገልጻሉ። አገልግሎቱን በጥራጥሬና ሌሎች ምርቶች ላይም በማስፋት ምርቶችን በጥራትና በወቅቱ ተጠቃሚው ዘንድ የማድረስ አቅም በመፍጠር የበለጠ ለመሥራት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዝግጁ እንደሆነም ተናግረዋል።

የጳጉሜን ሁለቱ ‹‹የአምራችነት›› መርሃግብር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ተጠቃሚን ተደራሽ እስከ ማድረግ የሚዘልቅ ቅንጅታዊ ተልዕኮን ለማስፈጸም መሰረት የተጣለበት ሊባል የሚችል ነው። መርሀ ግብሩ በተለያየ የግብርና ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ የአርሶ አደሮች አደረጃጀቶች የሆኑ ዩኒየኖች፣ በከተማ ግብርና ላይ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች፣ በእንስሳት፣ አትክልትና ልማት ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰሩ ባለሀብቶች፣ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ ምርታቸውን ለሚያቀርቡ በግብርና ሜካናይዜሽንና ኬሚካል ማምረት ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች የገበያ ትስስር ለመፍጠር መልካም አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## አዲስ ዓመትና አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ትግበራ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የኢትዮጵያ ትምህርት ዘርፍ ከሥርዓት እስከ አፈጻጸሙ ድረስ ከፍተቶች እንዳሉበት በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል። የባለሙያዎችም የዘወትር ጥያቄ እንደሆነ ይስተዋላል። ምክንያቱም በዘረፉ የሚታየው የሥርዓት እና የአፈጻጸም ክፍተቶች ኢትዮጵያውያንን ብዙ ዋጋ እያስከፈሏት ነው። አሁን ላለችበትና እየገጠማት ላለው ችግርም የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው ይህ ክፍተት የሞላበት አፈጻጸም እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

እስከዛሬ በነበረው የማስተማር ሥርዓት ውስጥ ሥነምግባር የሚባል ነገር አልነበረም። ከዚያ ይልቅ ትምህርቱ ትኩረት ያደርግ የነበረው ፖለቲካ ላይ ነው። ለዚህም ማሳያው በሥነምግባር ስም የሚሰጠው የሥ-ነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ሲሆን፤ ዋና ዓላማውም ፖለቲካው ትምህርቱ ላይ እንዴት ኃይል እንዳለው ማሳየት ላይ ያነጣጠረ ነው። ይህ ደግሞ የትምህርት ሥርዓቱን ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል አድርጎታል። ሥርዓቱን በአግባቡ ከመጠቀም ይልቅ ሥርዓቱ በአፈጻጸም ረገድ የፖለቲካ መጠቀሚያ ወይም የፖለቲካ ጥገኛ እንዲሆን በር ከፍቶለታል።

ዘርፉን ካለበት ችግር ለማውጣት ትምህርት ለሙያተኞች መተው እና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ አሠራር መከተል ምርጫ ብቻ ሳይሆን ግዴታ ቢሆንም ያም ሲደረግ አይስተዋልም። አሁን አሁን ግን ነገሮች እየተቀየሩ የመጡ ይመስላሉ። ከነበረው ችግርም ለመውጣት አንዳንድ እርምጃዎች ተጀምረዋል። ለምሳሌ፡- ፍኖተ ካርታ ተሰርቶ የትምህርት ሥርዓት አተገባበሩ ተፈትሾ በአዲስ መልክ ለመሥራት መታቀዱ አንዱ ነው። እስከዛሬ የታዩትን ችግሮች ይቀርፋል ተብሎ ታምኖበታልም።

ይህንን ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታ ለመተግበር ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሽርጉድ ከማለት አልፈው የሙከራ ተግባራቸውን እያጧጧፉ ነው። ከሙከራ ወጥተው ሙሉ ለሙሉ ወደሥራው ለመግባትም 2015 ዓ.ምን የሚጠብቁ ጥቂቶች አይደሉም። አዲሱ የትምህርት ዘመን በአዲሱ የሥርዓተ ትምህርት ትግበራ የሚጀመርበት ነው። እናም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ይህንን ተቀብለው በሙከራ ደረጃ ሲያከናውኑ ቆይተዋል። ያው ጦርነት ከነበረባቸው በስተቀር።

እንደ ኢዜአ ዘገባ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በአገር አቀፍ ደረጃ በተመረጡ 80 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሙከራ ትግበራ ለመጀመር ዝግጅት ተጠናቋል። በሙከራ ትግበራ አጀማመር፣ በተዘጋጁት የማስተማሪያ መጽሀፍትና በትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ የአሰልጣኞች ሥልጠና በደብረ ብርሃን ከተማ ተከናውኗል። በዚህ ወቅትም በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ማበልፀጊያ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ቴዎድሮስ ሸዋርገጥ እንዳሉት፤ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሥርዓተ ትምህርት ሪፎርሙ ግድ ነውና ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የሥርዓተ ትምህርት ሰነዶች የሚያካትታቸው የተማሪ ባህሪያት፣ የይዘት ፍሰት መርሀ ትምህርትና ሌሎች ዝግጅቶች ሲከናወኑ ቆይተዋል። በ2014 የትምህርት ዘመን በመላ ሀገሪቱ በተመረጡ 589 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲሱ የሥርዓተ ትምህርት የመማር ማስተማር የሙከራ ትግበራ ሲከናወን ቆይቷል።

ዶክተር ቴዎድሮስ፤ ከመስከረም ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮም እንዲሁ ከሙከራ በመውጣት በመላ ሀገሪቱ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ይተገበራል። በሁለተኛ ደረጃ ዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች ደግሞ በተመረጡ 80 ትምህርት ቤቶች የሙከራ ትግበራ ለመጀመር የሚያስችል ዝግጅት ተጠናቋል። ለዚህም የመማሪያና ማስተማሪያ መፅሀፍት ዝግጅት መደረጉን ያስረዳሉ። በ2016 ዓ.ም 11ኛና 12 ክፍል በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መስጠት እንደሚጀምር ጠቅሰው፤ ለዚህ ተግባር እውን መሆንም ከክልሎች ለተውጣጡ የትምህርት ባለሙያዎችና በሙከራ ትግበራ ለሚጀምሩ ትምህርት ቤቶች የአሰልጣኞች ሥልጠና እንደተሰጠ አስረድተዋል።

ከዚህ በፊት የነበረው የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ አጠቃላይ እውቀት ላይ ያተኮረ በመሆኑ የጥራት አግባብነት ችግር ነበረበት። በመሆኑም በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተቃኝቶ እንዲተገበር ይሆናል። ተማሪዎች ሀገር በቀል እውቀት እንዲኖራቸው የግብረ ገብና የሥነ- ምግባር ትምህርትን ጨምሮ የሥራና ተግባር ትምህርት ያካተተ በመሆኑ ብዙ ውጤት የሚታይበት ይሆናልም ብለዋል።

ይህንን አቅጣጫ ተከትለው ሥራቸውን ከጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አንዱ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ በ55 ትምህርት ቤቶች ላይ በሙከራ ደረጃ እየተተገበረ ይገኛል። ሥርዓተ ትምህርቱን በ2015 የትምህርት ዘመን በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም በቢሮው ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላት በኩል አስረድቷል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ትምህርት ሚኒስቴር በ2015 የትምህርት ዘመን በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የሙከራ ትግበራ እንደሚጀመር አስታውቋል። ስለሆነም እንደ ከተማ አስተዳደር አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የትምህርት ጥራትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ግብረ ገብነት፣ አገር በቀል እውቀት፣ ሙያና የቀለም ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ፣ ምርትና ተግባር፣ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የመንገድ ደህንነትና ሌሎች ትምህርቶችን ባካተተ መልኩ እንዲሰጥ ይደረጋል።

በ2015 የትምህርት ዘመን ደግሞ ሥርዓተ ትምህርቱን በሁሉም ትምህርት ቤቶች ለመተግበር ዝግጅት ተጠናቋል። በሙከራ ትግበራው ወቅት ትምህርት በአግባቡ መድረሱ ይረጋገጣል። ይህ ተሞክሮ ደግሞ ከዚህ ቀደሙ በነበሩት የተለያዩ ሥራዎች የታየና ብዙ መሻሻሎችን ያሳየ በመሆኑ ውጤታማ ያደርገናል። ለአብነት የ2013 የትምህርት ዘመን ኮቪድ-19ኝን በመከላከል መማር ማስተማሩ የተካሄደበትና ውጤት ማስመዝገብ የተቻለበት አንዱ ማሳያ ነው። በተመሳሳይ የተማሪዎች ምገባ፣ የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት ለትምህርት ውጤት መሻሻል አስተዋፅኦ ማበርከቱም ሌላው የሚጀመሩ አዳዲስ አሰራሮች ውጤት እንደሚያመጣ የሚያመላክት ነው። እናም በእነዚህና መሰል ተግባራት የተማሪዎች መጠነ ማቋረጥና መድገም ከቀነሰ እንዲሁም ጥራት ያለው ትምህር መስጠት ከተቻለ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ደግሞ የተሻለ ውጤት እንደሚመጣም እናምናለንና ጠንክረን የምንሰራ ይሆናል።

ሌላው አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት መተግበር ከጀመሩት መካከል የኦሮሚያ ክልል ሲሆን፤ ሥርዓት ትምህርቱ ትውልድን በዕውቀት፣ ሙያና ክህሎት ለማነፅ ትኩረት ያደረገ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱ ተማሪ-ተኮር እንዲሆን የሚያስችል በመሆኑ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የአይሲቲ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ እንደሚሰጥ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ዳይሬክተር ደረጀ ታደሰ ተገልጾ ነበር። በ2014 ዓ.ም ደግሞ በክልሉ ባሉ 75 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙከራ ደረጃ እንደተተገበረም አስረድተዋል።

የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የመማሪያ መጽሀፍቶችና የመምህራን ማስተማሪያ ሞጁሎች መዘጋጀታቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በኦሮሚያ ክልል በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ የግልና የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከመስከረም 09/2015 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚተገበርም የተዘገቡ ዜናዎች ያመላክታሉ።

ሌላው አዲሱን የሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ካስጀመሩ ክልሎች መካከል የደቡብ ክልል ሲሆን፤ የትምህርት ሥርዓቱ በ 161 ትምህርት ቤቶች በሙከራ ደረጃ ይተገበራል ብሎ እቅድ ይዟል። በደቡብ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የማህበራዊ ክላስተር አስተባባሪ እና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዲላሞ ኦቶሬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የትምህርት ሥርዓቱ በክልሉ ሀገር በቀል ዕውቀት ላይ ትኩረት አድርጎ የተዘጋጀ በመሆኑና ለሙያና ምርታማነት፣ ለሥራ ፈጠራ፣ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ያለው አስተዋዕጾ ከፍ ያለ በመሆኑ ከሙከራው ባለፈ ሙሉ ለሙሉ ወደሥራው እንዲገባ ይፈለጋል። በዚህም በሙከራ ደረጃ ባለፈው የትምህርት ዘመን በተለያዩ ቋንቋዎች በተዘጋጁ መጻህፍት በ115 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሲተገበር ቆይቷል። አሁንም በ2015 የትምህርት ዘመን በክልሉ ሙሉ ለሙሉ ይጀመራል። ለዚህ ደግሞ እንደ ክልል ዘርፉን የመደገፍ ሥራ ይሰራል። ከዚህ ባሻገር የፖለቲካ አመራሩ እና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላትም የክልሉን የትምህርት ገጽታ ለመቀየር የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከት አለበትና መነሳሳት ለመፍጠር ይሞከራል።

የመጨረሻ ያደረግነውና ልናነሳው የወደድነው ክልል የአማራ ክልልን ሲሆን፤ እርሱም እንደሌሎቹ ክልሎች የአዲሱን የትምህርት ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ዳይሬክተር አቶ ካሳዬ አባተ እንደገለጹትም፤ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ለማስተማር ዝግጅት ተጠናቋል። በክልል ደረጃም የማስተማሪያ መጽሀፍት ተዘጋጅቷል። በዚህም በተመረጡ 44 የአንደኛና በ17 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በሙከራ ደረጃ ለመተግበር ዝግጅት ተደርጓል። በትምህርት ቤቶቹ በሚጀመረው አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ከ77 ሺህ የሚበልጡ ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። እናም የሙከራ ትግበራው በኅዳር 2014 ዓ.ም ይጀመራል። ክልሉ ይህንን ቢልም ወደ ተግባሩ ለመግባት ግን የነበረበት ቁመና እንደፈተነው ማንም ይረዳዋል።

በእርግጥ የትምህርት ዘርፉ ቀደም ሲልም ብዙ ችግሮች ነበሩበት። አንዱ ከፖለቲካ ጥገኝነት በአግባቡ አለመላቀቁ ሲሆን፤ ሌላው በኮቪድ-19ኝ የተፈተነ መሆኑ ነው። ከዚያ ይባስ ብሎ ደግሞ የሰሜኑ ጦርነት ሁሉንም የባሰ አደረገው። የዚህን ጊዜ ደግሞ አማራና አፋር ክልሎች በተለየ ሁኔታ እንዲጎዱ ሆነዋል። በክልሎቹ በሺዎች የሚቆጠሩ የትምህርት ተቋማት በሕወሓት ታጣቂዎች ወድመዋል። የትምህርት ቁሳቁሶችም ተዘርፈዋል። የመፈናቀልና የሞት አደጋም እንዲሁ ቀላል አልነበረም። ስለሆነም በዘርፉ የተጀመረውን የማሻሻያ ጅማሮ ከግብ ለማድረስ እንዲቸገሩ አድርጓቸዋል።

እንደሚታወቀው ትምህርት በዓለም ላይ ለሚታዩ ለውጦች ጉልህ ሚና የሚጫወት፣ ለዕድገትና ለለውጥ ቀዳሚ መሠረት ነው። ትምህርትን በአግባቡ የተጠቀሙ እና ውጤታማ የትምህርት ሥርዓት የተከተሉ የዓለም አገራት በተለያዩ ዘርፎች ቀዳሚ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። የትምህርት ዓላማ ዕውቀትን ማስጨበጥ እና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሁለንተናዊ ዕድገት ማምጣት እንደሆነ ግልጽ ነው። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ታምኖ ወደተግባር ቢገባም አንዳንዶች ትግበራውን እውን እንዳያደርጉ ግን እንቅፋት ገጥሟቸዋል።

በችግሩም በትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለው ማሕበረሰብ መቅሰም ያለበትን ተገቢ ዕውቀት አግኝቶ መውጣት ሲገባው ራስን ማዳን ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲቆይ አስገድዶታል። ይሁን እንጂ በአለው አጋጣሚ ሁሉ ትምህርቱ ወደ ሙከራው እንዲገባ ይደረጋል መባሉ ተሰምቷል። ምክንያቱም ከጦርነቱ ጎን ለጎን የማስተማር ሥራው ሳይቋረጥ ሲያካሂድ እንደነበር ይታወቃል። እናም ችግሩ ያጋጠማቸውን ቦታዎች የተለየ ድጋፍ በማድረግ ወደ ሙከራ ተግባራቸው እንዲገቡ ማገዝ ያስፈልጋል። ያ ካልሆነ ግን ልዩነቶች ይፈጠሩና ትምህርት ሁሉንም የሀገራችንን ችግሮችና ጉድለቶች መሙላቱ እንዳይችል ይሆናሉ። ስለሆነም ተገቢነቱ፣ ጥራቱ፣ ችግሮቹና ጉድለቶቹ ላይ አይቶ መተጋገዝ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው ሳንል አናልፍም።

**ስትውስታ**

የትምህርት እና ሥልጠና ፍኖተ ካርታው የተሻሻለው የትምህርት ሥርዓት የመማር ማስተማሩን የጥራት ደረጃ ለማሻሻል፣ እንዲሁም ሙያዊ ግዴታውን በብቃት የሚወጣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የትምህርት ማሕበረሰብ መፍጠር የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት ነው። በዚህም መሰረት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ግብረ ገብነት፣ አገር በቀል ዕውቀት፣ ሙያና የቀለም ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ፣ ምርትና ተግባር፣ ጥናትና ምርምር ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ቅደመ አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ተከፋፍሏል።

በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ማሻሻያ ተደርጎባቸው ተግባራዊ እየተደረጉ ከሚገኙ መሻሻያዎች መካከል፣ ከ 1 እስከ 6ኛ ክፍል ላሉ የክፍል ደረጃዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንዲሰጥ፣ ከ 7እስከ 12ኛ ክፍል ሁሉም ተማሪ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲማር እና ከ 1እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ እንግሊዝኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት እንዲሠጥ የሚሉት ይገኙበታል።

በቀድመው የትምህርት ሥርዓት 10ኛ ክፍል ይሰጥ የነበረው አገራዊ የመልቀቂያ ፈተና እንዲቀር የተደረገ ሲሆን፣ አጠቃላይ ፈተና በክልል ደረጃ 6ኛ ክፍል እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ 8ኛ እና 12ኛ ክፍል ላይ ይሰጣል። ከዚህ ቀደም ሦስት ዓመት የነበረው የተማሪዎች የዩኒቨርስቲ ቆይታ ዝቅተኛው አራት ዓመት እንዲሆን ተደርጓልም። ለሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች በመጀመሪያ ዓመት ከሚሠጡ ትምህርቶች ውስጥ እንደ ጂኦግራፊ፣ አንትሮፖሎጂ፣ ሶሺዮሎጂና ሥነ-ምግባር የመሳሰሉት ተካተዋል።

# ‹‹ሕወሓት አሁን ደግሞ የጀመረው የአማራ ሕዝብን በቃላት መሸንገል ነው››

- ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

‹‹የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ›› የሚለው የአሸባሪ ሕወሓት ሰነድ በወርሃ ነሃሴ 2014 ዓ.ም ሾልኮ መውጣቱ ይታወሳል። በጽሁፉም ከአጋሮቹ ጋር የሚከተለውን ስትራቴጂ አስመልክቶ የሚተነትን ሲሆን፤ በየደረጃው ለሚገኝ አመራር ግብዓት እንዲሆን የቀረበ ስለመሆኑም መረጃው ያሳያል።

በዚህ ሰነድ እንዴት ኢትዮጵያን መቀመቅ እንከታለን ሲልም ሕወሓት ሴራ ለመሸረብ ሞክሯል። የሁኔታ ትንተና፤ መልካም ዕድሎችን ማስፋትና ፈተናን መቀነስ በሚለው ርዕሱ ስር €€የልዩነት ነጥቦችን በማሕበራዊ ሚዲያ በማጉላት አሃዳዊው የዐቢይ መንግሥት በአማራ ሕዝብ ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት እንዳይኖረው መሸርሸር ያስፈልጋል ሲል ያትታል።

በሌላ በኩል፤ ይሄ ጠባብ እና ተስፋፊ ሃይል በፍጹም የትግራይ አጋር ሲሆን እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል። ይሁንና ይህንን እውነታ በግልጽ ባለማሳየት በተመረጡና የጋራ ስራ ሲሰራባቸው የሚገቡ ጥቂት አጀንዳዎች በጥንቃቄ ሲቀረጹ ይገባል። በግልጽም ይሁን በስውር በፋኖ ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች መብዛታቸው የአማራ ክልል መንግሥትን የሚፈትን እንቅስቃሴ ይሆናል፤ ይህም ለትግራይ ካለው ፈተና ይልቅ መልካም እድል ይዞ የሚመጣ አጋጣሚ በመሆኑ ሚዛን የሚደፋ ነው። ስለሆነም ይህ ግንኙነት በከፍተኛ ጥንቃቄ ሲያዝ ይገባል‹‹ ሲል ይመክራል።

በአጠቃለይ በሰነዱ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መስተጋብሮችን በማናጋት የሥልጣን ጥማችን እንወጣለን ይላል የአሸባሪው ሕወሓት ሰነድ። በተለይም አማራን በማጥላላት ሥነልቦናውን ሊጎዳ ይችላል ብሉ ባሰበው መልኩ ይገልጻል፤ በዚህና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሕወሓትን አፈጣጠርና ታሪካዊ ሥሪቱን በማጣቀስ ከታሪክ ምሁሩ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ጋር ቆይታ አድርገናል።



**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን ከሕወሓት ሾልኮ በወጣው ሰነድ በተደጋጋሚ የአማራ ሕዝብን እንደ ጠላት ይፈርጃል። ስመሆኑ አማራን በተለየ ሁኔታ ለማየት ያስገደደው ታሪካዊ ሁኔታ ምንድን ነው ብለው ያስባሉ ?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-**እንግዲህ ይህን በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው በሕዝብ ደረጃ የትግራይ እና የአማራ ሕዝብ በታሪክ ጥላቻ ነበረው ወይ ብለን ማየት አለብን። በታሪክ ስንመለከት እነዚህ ሁለት ሕዝቦች በጣም ጠንካራ የሆነ ሃይማኖታዊ፣ ማሕበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ያላቸው ናቸው ። ሌላው ቀርቶ ተራው ሕዝብ ወይም ዜጋውን ተትን ባለአባቶችን ስንመለከት እርስ በእርስ ሲጋቡ የኖሩ ናቸው። ከግዛት ባለፈ ወዳጅነት ነበራቸው። ስለዚህ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ምንም የተለየ ጥላቻ የለም።

አሁን ከሕወሓት ሾልኮ በወጣው ሰነድ አማራ ላይ የሚንጸባረቀው ጥላቻ የመጣው ከምንድን ነው ስንል የራሱ ታሪክና አካሄድ አለው። ይሄ የሕወሓት ቡድን እንደ ቡድን ሲደራጅ ያመጣው ነው። የብሄር ፖለቲካ ሲነሳ ማጠንጠኛዎች አሉት። ለሥልጣን ለመብቃት አንድ ነገር መፈልግ አለበት። ወይንም ደግሞ የጦስ ዶሮ የሚሆን አካል ይፈልጋል። ስለዚህ ሕወሓትን ያቋቋመው ቡድን ጠላት ብሎ የተነሳው አማራን ነው ። ለራሱ ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ብሄር አማራ ጠላትህ ነው ብሎ ነው የተነሳ።

ሁለት ደረጃ ነበረው የመጀመሪው የአማራ ገዥ መደብ ነው የሚል አቀነቀነ። ከዚህም አለፍ ሲልና ትግል እያቀነቀነ ሲሄድ ለሌላኛም ጠንቀኛ ብሎ ለማሳየት አማራን መፈረጅ ጀመረ። ምንጩ ከሕዝብ ግንኙነት ሳይሆን ከፖለቲካ አደረጃጀቱ የመነጨ ነው። ይህ ነው በመላ ኢትዮጵያ 1983 ዓ.ም ጀምሮ በየሚዲያ እና ሕዝብ የተቀነቀነው። ይህ ሆን ተብሎ ታስቦ የተሰራበት ነው።

ሰሞኑን ሾልኮ የወጣው ሰነድም ያንን የማስቀጠል ነው። ሌላው ደግሞ ከአስተዳደራዊ ወሰን ጋር ጠላት ብሎ የሚመለከተውም የአማራን ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያዊ አቋም በመያዝና ኢትዮጵያን በማቀንቀኑ የትኛው ወገን ነው በሚለው ላይ ሲያነጣጥሩ አሁንም ዓላማቸው አማራን ሕዝብ የማዳከም ስልቶች ተንጸባርዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪ ሕወሓት ቡድን መግለጫዎች በብዛት አማራን በማስፈራራት ፤ ጥላቻን በመግለጽ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ሰሞኑን እንደሚሰማው፤ የአማራ ሕዝብ ወዳጆችን ነው የምናወራርደው ሂሳብ የምንነቅለው ሰንኮፍም የለም ሲሉ ይደመጣሉ። ይህን የሚያደርጉት ለምን ይመስሉታል ?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** እንግዲህ እነዚህን መግለጫዎች ልብ ብሎ መመልከት ይገባል። ፕሮፓጋንዳ በሁሉም ቦታ እና ፖለቲካ ዘንድ አለ። የሕወሓት ፕሮፓጋንዳ እኩይ ፕሮፓጋንዳ ነው። ይህ አንዱን በሌላው ላይ ለማስነሳት የሚጠቀምበት ስልት ነው። እውነተኛ ፕሮፓጋንዳ ግን አንድን በጎ ነገር ይዞ ሕዝብ እንዲያውቀውና እንዲቀበለው ማድረግ ነው።

ስለዚህ የሕወሓት መግለጫዎች እኩይ ነገሮችን ይዞ የተነሳ ነው። በዚህ ውስጥ ወጥ የሆነ ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ አይቻልም። በዚህ የእኩይ ፕሮፓጋንዳቸው ውስጥ አማራን ጠላት አድርጎ ፈርጇል። ሌላ ጊዜ ወዳጅ አድርገው ይሄዳሉ። ለመሆኑ እየጨፈጨፉት የነበረው አማራ ሕዝብን አልነበረም። ሌላ ቦታ ሲያስጨፈጭፉ የነበረውም ይህን ሕዝብ አይደለም። ስለዚህ ጉራማይሌ ብቻ ሳይሆን እኩይ ሲሆኑ የሚታይ ባህሪ ነው። ሕወሓቶች ከተፈጥሮ ባህሪያቸው የተነሳ ይህን የሚያደርጉ ናቸው። የሕወሓት ሰዎችም በባህሪቸው በጣም ውሸት ያበዛሉ። ለዚህም ሲሉ አንድ ጊዜ ጠላት ብለው የፈረጁትን ሌላ ጊዜ ወዳጅ አድርገው ይገልጹል። አሁን የጀመሩት አማራ ሕዝብን በቃላት መሸንገል ነው።

የሕወሓት ሰዎች መግለጫዎች እንድ ሕዝብ አማራን ጠላት ብሎ ከፍረጃ ካልወጣ እና ሕወሓት አማራ ላይ ያለውን አቋም ካልቀየረ መግለጫዎች ለውጥ አያመጡም።

**አዲስ ዘመን፡ በሰነዱ ከተገለጹት ውስጥ በአማራ መካከል ያለውን ልዩነት ማስፋትና ክልልነት ጥያቄዎች ጋር የሚነሱትን በማንሳት ግጭት ማቀጣጠል የሚለውን እሳቤ እንዴት አዩት?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** ጦርነት የሚያነሳ አካል አንድ ትልቅ ሥራዬ ብሎ የሚሰራው ነገር አለ። ይህም ዲሞብላይዜሽን ነው። ይህ ማለት ሕዝብና መንግሥት አንድ እንዳይሆን ማድረግ ነው። በሁለቱ አቅም እንዳይፈጥር ክፍፍል እንዲኖር ይሰራሉ። አንደኛው ሕዝብና መንግሥትን መነጣጠልና ማቃቃር አጀንዳ መፍጠር ላይ ይተጋሉ። ሁለተኛው ደግሞ ሕዝብም እርስ በእርሱ መጠራጠርና መከፋፈል እንዲፈጠር ይፈልጋሉ። እነዚህ ስሜቶች እንዲኖሩና አንድነት እንዳይኖር ማድረግ ነው። በአሁኑ ወቅትም ጦርነት ለመጀመር ያነሳሳቸው ይህን የተሳሳተ የፖለቲካ ትንተናና ስሌት በመያዝ ነው።

አሁን ባለው ሁኔታም በአማራ ክልል ፋኖዎች ስለታሰሩ፤ በመንግሥትና በፋኖዎች ብሎም በሕዝብ መካከል ክፍተት ስላለ ሕዝብን ለማነሳሳት አይቻለውም። ስለዚህ አቅማችንን አጠናክረን ብናጠቃ የሚመክተን አካል የለም በሚል ስሌት ነው። ስለዚህ እየተሰራ ያለውና አሸባሪው ህወሓት እየተጠቀመ ያለው ይህን ስሌት ነው። በአንድ በኩል በፕሮፓጋንዳ ፋኖን የመኮነን ሥራ ይሰራል። በሌላ በኩል ደግሞ የክፍተት ምንጭ አድርጎ ለመጠቀም ይፈልጋል። ይህን በግልጽ አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ያለ ቡድን ነው።

> የሕወሓት ሰዎች መግለጫዎች እንድ ሕዝብ አማራን ጠላት ብሉ ከፍረጃ ካልወጣ እና ሕወሓት አማራ ሳይ ያለውን አቋም ካልቀየረ መግለጫዎች ለውጥ አያመጡም

ሁለተኛው ደግሞ አካባቢያዊ አስተዳደሮች ላይ ሕዝብ እምነት እንዲያጣ ማድረግን ዓላማ አድርገው እየሰሩ ነው። ለምሳሌ የአማራ ክልልን የልዩነት ነጥቦችን ወስዶ የማዳከም ሥራ ነው እየሰሩት ያሉት። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝባዊ ተቀባይነት እንዲያጣ ማድረግ ነው። በዚህም መንግሥት ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ እንዲሆንና ይህን አጠናክረው እንደሚሰሩ የታወቀ ጉዳይ ነው።

የፖለቲካ ነበልባል የሚያስነሱ ጉዳዮችን ለራሳቸው ጥቅም ለመቀየር ይጥራሉ። ለምሳሌ በደቡብ አካባቢ ያለውን ጉዳይ በተለይም ከክልል አደረጃጀት ጋር ያለውን ሁኔታ ለማገዝ የቆሙ መስለው ነገሮችን ማባባስ ይፈልጋሉ። በዚህም እንቅስቃሴያቸው ወትሮም እኛ እንሻል ነበር ለማለት የሚሰሩት ነው። ወቅታዊ የፖለቲካ ንፋስ የሚያመጣቸውን ነገሮች በደንብ ነዳጅ በመስጠት መንግሥትን በተለያየ ነገሮች መወጠር፣ አቅሙን ማዳከም፣ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነቱ እንዲወርድ የማድረግ ስልትና ስትራቴጂ ነው። ዋነኛ ሥራው ወይንም ድምር ውጤቱ የመንግሥትን ተቀባይነት ማሳጣት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሕወሓት የሴራ ሰነድ ውስጥ የተፈጠረውን የኑሮ ውድነትን ማባባስና የኢኮኖሚ አሻጥር ማባባስና አርሶ አደር ምርት እንዳይሰበሰብ ማድግ የሚል አለው። ይህን ከቡድኑ የቀድሞ**

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

ባህሪ ጋር እንዴት ያዩታል?

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** እንደሚታወቀው ክረምት ማለት በተለይም ደግሞ ከሰኔ ጀምሮ እስከ ታህሳስ ያለው ለአብዛኛው የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ወሳኝ ወቅት ነው። ይህ በብዛት የስራና የምርት ወቅት ነው። የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህልውና በዚህ ወቅት ላይ የተመሰረተ ነው። አርሶ አደሩ የሚለፋበት ጊዜ ነው። ስለዚህ ጦርነቶችንና ግጭቶችን መቀስቀሱ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። ዝምብሎ አመቸኝ ብሎ አይደለም የተነሳው። ሌላው ሕዝቡን በመንግሥት ላይ ማስነሳት የሚቻልበት ትልቁ ነገር የኢኮኖሚ ዋስትናውን ዜሮ ማድረግ ነው።

ስለዚህ አሸባሪ ሕወሓት በአማራ ክልል ላይ ያለው ስትራቴጂ የእርሻ ስራ በወቅቱ እንዳይሰራ ማስተጓጎልና እርሻውን በሙሉ ማደናቀፍ ነው። አርሶ አደሩን ከሥራ ውጭ ማድረግ ነው። በተለያየ መንገድ ተፈናቃይ ማድረግ ነው። ይህ ሥራ በጣም አደገኛ ነው። ከርሃብና ችጋር በላይ የሰው ልጅ የሚፈራው ነገር የለም። ስለዚህ ይህን እንደ ፖለቲካ ስልት መጠቀም ይፈልጋሉ። ህወሓትም ይህን እያረገ ነገሮችን ማናጋት ይፈልጋል። እንደፖለቲካ ስልት መጠቀም ይፈልጋል፤ በእቅድም የሚሰራው ነው። ርሃብ ሲኖር ሰዎች በመንግሥት ላይ ያምፃሉ። በዚህ ጊዜ ግለሰብና መንግሥትን ማናጋት ይፈልጋሉ። ይህን እንደ አዲስ ስትራቴጂ እየተጠቀሙበት ነው። ይህን ባለፈው ዓመትም አድርገው አሳይተዋል። ባለፈው ዓመት በወረራም አረጋግጠዋል። ሌላው ቀርቶ ኢኮኖሚ ዋስትና የሆኑ እንስሳትን ጭምር ገድለዋል። እንስሳት ፖለቲካውን አያውቁም። ይህ ዋነኛ ዓላማው ኢኮኖሚውን ማናጋትና መሰረቱን ማዛባት ነው። ስለዚህ ድንገት የተካሄዱ ሳይሆን በደንብ ተጠንተው የተካሄዱ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ሕወሓት ከፌዴራል መንግሥት ጋር ውይይት እፈልጋለሁ ቢልም፤ አፍሪካ ሕብረትን ጨምሮ አፍሪካዊ ተቋማትን ያጣጥላል። ይህን ለምንድ ማድረግ ፈለገ?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-**ሕወሓትከመጀመሪያው ሲነሳ በአፍሪካ ደረጃ የነፃነት ቡድን አይደለም። እዚህ ግባ የሚባል ቡድንም አይደለም። ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት ነፃ ሲወጡ የዓርነት እንቅስቃሴዎችና ጦርነቶችን አካሂደዋል። የሕወሓት ከዚህ አኳያ ሲታይ ምንም ስያሜ ለመስጠት የሚያስቸግር ነው። ስለዚህ ለመሰል ቡድን በርካታ አፍሪካ ሀገራት የዲፕሎማሲም ሆነ የፖለቲካ ድጋፍ አይሰጡም ነበር።

ለሕወሓት ቡድን ዓላማ እና አካሄድ ግልጽ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩት ጥቂት አገራት ሲሆኑ እነዚህም ግብጽ፣ ሱዳን እና ሶማሊያ ናቸው። ሶማሊያ በትጥቅም በምንም ሳይሆን ፓስፖርት በመስጠትና በመሳሰሉት ያግዙ ነበር። ይህን ሲያደርጉ የነበረውም በወቅቱ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ጋር ካላቸው ቁርሾ እና የውሃ ፖለቲካም ጋር በተያያዘ ነው። ከዚህ በተረፈ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ለሕወሓት ፖለቲካ ባይተዋር ናቸው፤ ምንም አይፈልጉም።

ከእነዚህ ይልቅ ሕወሓት ገና ጡጦ መጥባት ሲጀምር ጀምሮ ‹አይዞን አለን› ሲሉ የነበሩት ምዕራባውያን ናቸው። ይህም የሆነው እነዚህ የሕወሓት ደጋፊዎች የነበሩትም ምዕራባውያን የራሳቸው የፖለቲካ ፍላጎት ስለነበራቸው ነው ። ወደ ሥልጣን ለመምጣት ዋዜማው ላይ ሆኖም፤ ሥልጣን ላይ ከመጣ በኋላ እና ከሥልጣን ማግስትም ሕወሓት ያደረገው የአፍሪካ ፖለቲካ ጉዳዩ አይደለም። ከአፍሪካውያን ጋር አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እዚህ ግባ የሚባል ሥራ አይሰራም። ይልቁንስ በፖለቲካም በኢኮኖሚም ትልቅ ድጋፍ አድርጎና ይበጀኛል ብሎ የወሰደው አውሮፓውያንንና አሜሪካን ያሉ የምዕራባውያንን ሃይል ነው። በእርግጥ አሁንም እየደገፉት ያሉት እነርሱ ናቸው። ይሁንና ኢትዮጵያ ያካሄደችውን አፍሪካ ወንድሞቻችን በጣም በደስታ የተቀበሉት ጉዳይ ነው።

ስለዚህ አሸባሪው ሕወሓት አፍሪካ ሕብረትን በአደራዳሪነት ያለመቀበሉ ምክንያት፤ አፍሪካውያን ችግራቸውን የሚመለከቱት ከሃቅ አኳያ በመሆኑ ነው። ከግብጽ እና ሱዳን በስተቀር አንድ የአፍሪካ ሀገራትን ብንወስድ የአፍሪካ ችግር ይፈታ የሚሉት እውነታውን ይዘው ነው። ሁኔታዎችን የሚያዩት ደግሞ እንደ አፍሪካ ሕብረት ሀገርነቷ ነው። ሌላው ደግሞ ከኢትዮጵያ የሚያጋጫቸው ነገር የለም። ምዕራባውያን ግን ብዙ ጥቅሞችና የፖለቲካ ፍላጎቶችን ያራምዳሉ። ይህን በደንብ ሸክፎ እና ታዛዥ ነኝ ብሎ ራሱን ያዘጋጀው ሕወሓት ነው።



**አሁን ከሕወሓት ሾልኮ በወጣው ሰነድ አማራ ላይ የሚንጸባረቀው ጥላቻ የመጣው ከምንድን ነው ስንል የራሱ ታሪክና አካሄድ አለው። ይሄ ጥላቻ የሕወሓት ቡድን እንደ ቡድን ሲደራጅ ያመጣው ነው። የብሄር ፖለቲካ ሲነሳ ማጠንጠኛዎች አሉት። ለሥልጣን ለመብቃት አንድ ነገር መፈለግ አለበት። ወይንም ደግሞ የጦስ ዶሮ የሚሆን አካል ይፈልጋል። ስለዚህ ሕወሓትን ያቋቋመው ቡድን ጠላት ብሎ የተነሳው አማራን ነው ። ለራሱ ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ብሄር አማራ ጠላትህ ነው ብሎ ነው የተነሳው**

ሕወሓት ብሄራዊ ጥቅም የሚባል ነገርን አያስብም። ሕወሓት ከፖለቲካ ጥቅሙ ውጭ፤ ብሄራዊ ጥቅምን ከግምት ውስጥ አስገብቶ አያውቅም። ብሄራዊ ጥቅምን የማያስቀድም ደግሞ እንኳን ለሀገር ለራሱ ህልውና መቀጠሉም አጠራጣሪ ነው። ይህ ቡድን ለማነው የሚቆመው፤ እንዴት ነው ሀገርን ሊወክል የሚችለው፣ እንዴት ነው ሕዝብን የሚጠቅመው? ስለዚህ ሕወሓት የብሄራዊ ጥቅም ጉዳይ አያነሳም። የምዕራባውያን ጉዳይ ለማስፈጸም ምንም አያቅማማም። እነርሱ ደግሞ ይህንን በጣም ይፈልጉታል። ሕወሓት ያላግጣል። አፍሪካ ትልቅ አቅም አለው። ምዕራባውያንን ድረሱልኝ፤ ይህን ሆንኩ ብሎ ማለቃቀስ፤ የረድዔት ድርጅቶችን የሚጣሩበት ምክንያት ሥር መሰረታቸውና ባህሪያቸው ይህ ስለሆነ ነው። ለዚህም ሲባል ይፈልጉታል።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪ ቡድን ከሚያሳያው ባህሪ በመነሳት ለትግራይ ሕዝብ መብት፣ ነፃነት፣ ጥቅም፤ እኩልነት፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ማበብ የቆመ ነው ማለት ይቻላል?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** ሕወሓት አይደለም ለትግራይ ሕዝብ ለራሱ ውስን ቡድን በአግባቡ የሚቆም አይደለም። የተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ እንደፈለጉ የሚያሾሩት፤ የሚያደርጉትና የፖለቲካ ፍላጎታቸውን የሚያራምዱበት ነው።

ለትግራይ ሕዝብ ቢቆም ኖሮ፤ የትግራይ ሕዝብ የሚፈልገው ኢትዮጵያዊነትና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብሮ መኖርን ነው። ተጋብቷል፤ ተዋልዷል። የኢኮኖሚ ትስስር አለው፤ የሚጋራው ማሕበራዊ ሥነ-ልቦና አለው። በጣም ሰፊ ነው። በተለያየ የኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ንብረት አፍርቶ፤ ትዳር መስርቶ ሥራ እየሰራ የሚኖር ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ትግራይ እንዲህ ነው እያሉ ሌላ ፖለቲካ ማንሳት ለትግራይ ሕዝብ መቆም አይደለም።

በመጀመሪያ የፖለቲካ ነፃነት የተነፈገው የትግራይ ሕዝብ ነው። በመጀመሪያ የመደራጀት ነፃነትና መብት የተነፈገው የትግራይ ሕዝብ ነው። ትግራይ ውስጥ የእውነት ነፃነት እንዲመጣ፣ ዴሞክራሲ እንዲያድግ፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን አለፍ ብሎም ትግራይ ውስጥ ሕዝቡ ነፃነት ይኑረው ካልን ለምን የሕዝብ ጥያቄ ማፈን አስፈለገ?

ነፃ በሆነ መድረክ ላይ የፖለቲካ መድረክ እንዲፈጠር ለምን አያደርግም? ትልቁ የሕወሓት ችግር ለትግራይ ሕዝብ ከእርሱ ውጭ ወይንም የእርሱን አጀንዳ የሚያቀነቅን አምሳያ የሆነ የፖለቲካ ኃይል ካልሆነ በስተቀር ሌላ እንዲበቅል አይፈቅድም።

ይህን ወትሮም ሲሰራ ነበር። ከ2010 ዓ.ም በፊትም ሆነ ከዚያን በኋላ ይህን ሲሠራ ነበር። ስለዚህ ለትግራይ ሕዝብ ቆመ የሚባለው ነገር፤ ራሱ የትግራይ ሕዝብ ያውቀዋል። ለትግራይ ሕዝብ ቆሜያለሁ ቢልም «ሆድ ሲውቅ ዶሮ ማታ» የሚሉት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪ ቡድን በዚህ ደረጃ የትግራይ ሕዝብን የሚጨቁን ከሆነ ሕዝቡ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** የትግራይ ሕዝብ ማድረግ ያለበት ለሕወሓት ማርከሻውና ፍቱን መድሃኒቱ ራሱ ነው። በእርግጥ በሃይል ተገዶ የተያዘ ሕዝብ ነው ይታወቃል። የሕወሓት አደረጃጀት ቀላል የሚባል አልነበረም። የትግራይ ሕዝብ በግድ አጥሮ ነው የያዘው። ሆኖም መሆን ያለበት በትግራይ ክልል የሚኖርም ሆነ ከሀገር ውጭና በሌሎች ቦታዎች የሚኖር የትግራይ ተወላጅ ይህንን መኮነንና ሕወሓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ እና ከትግራይ የፖለቲካ መድረክ እንዲገለል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት። እንዲሁም ከሀገር ውጭ የሚኖረው የትግራይ ተወላጅ ይህን ማወቅ አለበት፤ በጥቂት የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ መፈታት የለበትም። እዚህ ላይ ጠንክረው መስራት ይኖርባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የረድኤት ድርጅቶች፣ ምዕራባውያንና ሌሎችም አሸባሪ ሕወሓት አማራ እና አፋር ክልሎችን የሚፈጽውን ወረረራና ግፍ ብሎም ሕፃናትን ለጦርነት ሲማግድ በዝምታ ያልፉሉ። ይሁንና በመንግሥት የመከላከል እርምጃ ሽንፈት ሲከናነብ ሁሉም በአንድ ላይ ይረባረባሉ፤ መግለጫ ያወጣሉ፤ ያግዛሉ። ይህን ማድረግ ለምን አስፈለገ?**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** ይህን ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ያውቃሉ። ሕወሓት ለሕዝብ የመጣን እርዳታ ለጦርነት ሲያውል ይህ የመጀመሪው አይደለም። ወትሮም ገና እየታገልኩ ነው ሲልም 1977 ዓ.ም ያደረገው ነው። በረድዔት ሥም ደግሞ ሲዘርፍ ነበር። በ1977 ዓ.ም ሆነ አሁንም እያደረገው ነው። እርዳታው ለትግራይ ሕዝብ ደርሷል ወይ ለሚለው፤ በማያጠራጥር ሁኔታ አከፋፋዩ ሕወሓት ነው፤ ሰጪና ነሺውም ሕወሓት ነው። ስለዚህ ለደጋፊውና ለሚዋጋላት ይሰጣል። በአጭሩ ሕወሓት መፈክር አውጥቷል። ይህም «ለመብላት መዋጋት» የሚል ነው። ወጣቱንና ሕፃናቱን የሚያሰልፈው በዚህ መልኩ ነው።

ምዕራባውያንን ለምን አልኮነኑትም ለሚለው፤ ዓላማቸውን ያውቁታል። በአንድ በኩል እየሰሩ ያሉትም ይህ እንዲሆን ነው። የሰው ልጅ መራብ፣ ሰብዓዊነትና የሰው ልጅ መጎሳቆል ሙሉ ለሙሉ አስገድዷቸው ነው የሚል እምነት የለኝም። ስለዚህ ይህንን ምዕራባውያን ያውቁታል። ሁለተኛው የሕወሓትን አጥፊነት ሳያውቁት ቀርተው አይደለም። አማራ እና አፋር ክልል ሲወረር ጉዳያቸው አይደለም። ይህ ለምን ሆነ ስንል የፖለቲካ ዓላማቸው ስለሆነ ነው። ኢትዮጵያ ጠንክራ እንዳትወጣ ይፈልጋሉ። ነገ ከነገ ወዲ ኀልታ ከወጣች ለአፍሪካም ዓርዓያነቷን ብሎም በአካባቢዋ ብሄራዊ ጥቅሟን እነደምታስከብርና በምስራቅ አፍሪካ የሚኖራት ሚና እንዲኮስስ ብሎም ከሌሎች ጋር ተባብራ ሰርታ ከፍ እንዳትልና ሁነኛ ኢትዮጵያን ስለማይፈልጉ ነው። ስለዚህ የምዕራባውያን ዝምታው ምንድን ነው ቢባል ነገሩን እያወቁ ዓይን እንደመጨፈን፤ ጆሮ እንደመድፈንና አፍን ከመዝጋት የሚመጣ ነው። ይህ አሁን ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊትም በነበሩት የታየ ነው። ሀገር ሲሆን ለምሳሌ ሕወሓት ሀገርን በሚያስተዳድርበት ወቅት ከኤርትራ ጋር ጦርነት ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሲነሳ ያደሉት የነበረው ወደ የት ነው? ሕወሓት ሥልጣን ላይ በነበረ ጊዜ እና ኢትዮጵያ ሲል ከኤርትራ ጋር እኩል ማዕቀብ ይጥሉ ነበር። አሁን ግን ብቻውን ሲሆንና የእነርሱን ዓላማ ሲያስፈጽም ደግሞ ዝም ይባላል። የሕወሓት ጭፍጨፋ አይነሳም። ይህን እያወቁ ማውገዝ አልፈልጉም። ይሁንና የኢትዮጵያ ኃይል ሲጠናከር ምንም ማድረግ አይፈልጉም።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ሥም እናመሰግናለን።**

**ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



## ዜሌንስኪና ብሊንከን ዩክሬን ውስጥ ተወያዩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜሌንስኪ ትናንት በድንገት ዩክሬን ከገቡት የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንተኒ ብሊንከን ጋር ተገናኝተው መወያየታቸው ተነገረ፡፡

"ሩሲያን እንደ አሸባሪ አገር" መፈረጅን ጨምሮ በተለያዩ ጉዳዮች መነጋገራቸውን ዜሌነስኪ በየዕለቱ ምሽት በሚያሰሙት የትናንቱ ንግግራቸው አስታውቀዋል፡፡

ዜሌንስኪ በዚሁ ንግግራቸው "የህግ እውነታው ሁልጊዜም ከተጨባጩ እውነታ ጋር አብሮ መታየት አለበት፡፡ እውነታው ሩሲያ በዓለም ትልቋ የሽብርተኝነት ምንጭ እየሆነች መጥታለች፡፡" ብለዋል፡፡

"የሩሲያ ሽብር በዝምታ የማይታለፍ ስለመሆኑ ዓለም ከወዲሁ በማያሻማ መልኩ ምልክቱ ሊደርሰው ይገባል" ሲሉም አክለዋል ዜሌንስኪ፡፡

ከነሐሴ 26 ጀምሮ ከአንድ ሺ ስኩዌር ኪሎ ሜትሮች በላይ የሚሆነውን የአገራችን ግዛት ነጻ አውጥተናል በማለት የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ "ይህን ላስቻሉት ሁሉ ምስጋኔዬን አቀርባለሁ፡፡ በእነኚህ ቀናት የዩክሬን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብሎ እንዲናለበለብ ያደረጉቱን ሠራዊቱን፣ የደህንነት ሠራተኞቻችንን የልዩ ልዩ ኃይሎቻችንን ሁሉ አመሰግናለሁ" ብለዋል፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከንም ከዜሌንስኪ ጋር ከተወያዩ በኋላ በሰጡት መግለጫ "በግንባር የሚገኙት አስደናቂዎቹ የዩክሬን ተከላካዮች ለአገራቸው የሚያደርጉትን ፍልሚያ በጀግንነት ይቀጥሉበታል" ብለዋል፡፡

"የፈለገውን ያህል ጊዜም ቢፈጅ" ዩናይትድ ስቴትስ ለዩክሬን የምትሰጠውን ድጋፍ ትቀጥላለች በማለት ፕሬዚዳንት ባይደን የገቡትንም ቃል ከፍተኛው የዩናይትድ ስቴትስ ዲፕሎማት በመግለጫቸው በድጋሚ አረጋግጠዋል፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ ለዩክሬንና "በወደፊቱ የሩሲያ ወረራ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ ለተባሉ" ሌሎች 18 አገሮች የ2.2 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ለዩክሬን ደግሞ በቀጥታ 675 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተጨማሪ የጦር መሳሪያዎች በእርዳታ እንደምትሰጥ ትናንት ሀሙስ ማስታወቋ ተመልክቷል፡፡

**ምንጭ- ቢቢሲ**

## የአሜሪካ ጦር ስተፈጸመበት የሮኬት ጥቃት የመልስ ምት ሰጠ

በጋዜጣው ሪፖርተር




አዲስ አበባ፡- በሰሜን ምስራቅ ሶሪያ በሚገኙ ሁለት የአሜሪካ ጦር ይዞታዎች ላይ በሮኬት ጥቃት ለመፈጸም የዋሉ ናቸው የተባሉ መሳሪያዎችን ማውደሙን የአሜሪካ ጦር ትናንት አስታውቋል።

የአሜሪካ ማዕከላዊ እዝ የለቀቀውን መግለጫ ጠቅሶ የቪኦኤው ክሪስ ሃናስ እንደዘገበው፣ በአጥቂ ሄሊኮፕተሮች በታገዘው ድብደባ ሁለት ወይም ሦስት የሚሆኑና በኢራን እንደሚደገፉ የሚጠረጠሩ ሚሊሺያዎች ሲገደሉ ለሮኬት ማስወንጨፊያ የዋሉ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች መሳሪያዎች ወድመዋል።

አንድ የአሜሪካ ጦር አባል ለቀላል ጉዳት ህክምና እንደተደረገለትም ሪፖርቱ ጠቁሟል።

"ዩናይትድ ስቴትስ ከኢራን ጋር ግጭት ውስጥ መግባት አትፈልግም፤ ሰዎቻችንን ለመከላከል ግን አስፈላጊውን እርምጃ እንወስዳለን" ብሏል መግለጫው።

በምስራቅ ሶሪያ የሚገኙ ከኢራን እስላማዊ አብዮታዊ ዘብ ጓድ ጋር ግንኙነት ያላቸው ቡድኖች ሲጠቀሙበት የነበረን መሳሪያ ማከማቻና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ መሰረተ ልማቶችን ከአየር መደብደቡን የአሜሪካ ጦር ትናንት ማክሰኞ አስታውቆ ነበር።

ኢራን ከተጠቀሰው ቦታ ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም ስትል ትናንት ገልጻለች።

በሶሪያ የእርስ በእርስ ጦርነት የኢራን ሃይሎች የፕሬዚዳንት ባሽር አል-አሳድ ሃይሎችን በመደገፍ በሀገሪቱ ይገኛሉ።

በኩርዶች ከሚመራው የሶሪያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በመሆን የኢስላሚክ ስቴት ወይም የእስላማዊ መንግሥት ቡድኖችን ለመውጋት አሜሪካ 900 የሚሆኑ ወታደሮቿን አስፍራለች።

**ምንጭ፡- አሶሼትድ ፕሬስ**

ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# እንኳን አደረሳችሁ!

ለመላው ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርቱ ማሕበረሰብ እንዲሁም ለትምህርት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ሠራተኞች የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር እንኳን ለ2015 አዲስ ዓመት በሰላም አደረሰን ፤ አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ሲገልጽ በደስታ ነው !

በጦርነቱ የወደሙ የትምህርት ተቋማትን መልሰን ለመገንባት በምናደርገው ጥረት ላደረጋችሁት እና ለምታድርጉት ድጋፍ ከወዲሁ እያመሰገንን በአዲሱ ዓመት በትምህርቱ ዘርፍ ላይ የተሻሉ እና ውጤታማ ሥራዎችን በመሥራት የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለመፍጠር እና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን እንተጋለን !

አዲሱ ዓመት በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት የምንተገብርበት፣ በጦርነቱ የወደሙ ትምህርት ቤቶችን በተሻለ ደረጃ የምንገነባበት፣ የምገባ እና ሌሎች ፕሮግራሞችን አጠናክረን የምንቀጥልበት ይሆናል።

በከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ የመውጫ ፈተናን እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ ነጻነት ትግበራ ጨምሮ በርካታ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ሥራዎችን ከግብ ለማድረስ ከትምህርት ማሕበረሰቡ ጋር በቅርበት እንሰራለን።

በቀጣይ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በምናደርገው ጥረት ውስጥ መምህራን፣ ተማሪዎች እና መላው የትምህርቱ ማሕበረሰብ አብሮነታችሁ እንደማይለየን እያመንን የወደሙ ትምህርት ተቋማት ግንባታን ለመደገፍ የምታደርጉትን እገዛ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ እንጠይቃለን ! ።

**የተሻለ ትምህርት ፤ ለተሻለ ትውልድ!!**

**መልካም በዓል**

**የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ከ23 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ዝግጅቱን ቀጥሏል

**ብርሃን ፈይሳ**

በመጪው የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት አጋማሽ በሞሮኮ አስተናጋጅነት ከ23 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ይካሄዳል። በዚህ ውድድር ለመሳተፍ የማጣሪያ ጨዋታዎች ከመጪው ሳምንት ጀምሮ ይከናወናሉ። ሶስት ዙር ባለው በዚህ የማጣሪያ ፍልሚያ ላይም 38 ሀገራት ተካፋይ ናቸው። በዚህ ውድድር የሚሳተፉትም ስምንት አገራት ናቸው። በአፍሪካ ዋንጫው ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ ይዘው የሚያጠናቅቁ አገራትም እአአ በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ተካፋይ ይሆናሉ።

በአፍሪካ ዋንጫው ለመሳተፍ ዝግጅት እያደረጉ ከሚገኙ ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ስትሆን፤ የመጀመሪያውን የማጣሪያ ጨዋታም ከ10 ቀን በኋላ በሜዳዋ አበበ ቢቂላ ስታዲየም ታከናውናለች። ለዚህ የማጣርያ ጨዋታ የቡድኑ አዲስ አሰልጣኝ ሆነው የተሾሙት አጥናፉ ዓለሙ እና ረዳቶቻቸው ለ36 ተጫዋቾች ጥሪ በማድረግ ከነሐሴ 24/2014ዓም ጀምሮ በካፍ የልህቀት ማዕከል ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚም ከመቻል ስፖርት ክለብ ጋር የአቋም መፈተሻ ጨዋታ አድርገዋል። ይሁንና በዋናው ብሄራዊ ቡድን ለቻን ማጣርያ ጨዋታ የተካተቱ፣ በክለቦች አህጉራዊ ተሳትፎ ዝግጅት እና ክለቦች ተጫዋቾች ባለመልቀቃቸው ምክንያት ስብስቡ የተሟላ አልነበረም።

አሁን ግን ጨዋታው ቀናት ብቻ የቀሩት በመሆኑ አሰልጣኙ ለኢትዮጵያ ቡና እግር ኳስ ተጫዋቾች ቡድኑን እንዲቀላቀሉ በድጋሚ ጥሪ አቅርበዋል። እነርሱም ኃይለሚካኤል አደፍርስ፣ ጫላ ተሺታ፣ ብሩክ በየነ እና መሃመድ ኑር ናስር መሆናቸውን ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ሌላኛው የክለቡ ተጫዋች አማኑኤል ዮሐንስ እና የወላይታ ድቻ የተከላካይ መስመር ተጫዋቹ ሳሙኤል ተስፋዬ በአዲስ መልክ ጥሪ የቀረበላቸው ተጫዋቾች ሆነዋል።

ከክለቦች ተጫዋቾችን አለመልቀቅ ጋር በተያያዘም አሰልጣኝ አጥናፉ በሰጡት አስተያየት፤ ክለቦች ሀገራዊ ገጽታውን መመልከት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ ባለችበት ነባራዊ የእግር ኳስ ደረጃ ሰፊ የዝግጅት ጊዜ መውሰድና ጨዋታውም በቅርብ ሚደረግ እንደመሆኑ ሀገራዊ ጉዳይን ማስቀደም ተገቢ ነው። ውድድሩ የኦሊምፒክ ውድድር እንደመሆኑ ወጣት ተጫዋቾች በእግር ኳስ ወኪሎች (ኤጀንቶች) የመታየት ዕድላቸው የሰፋ በመሆኑ ራሳቸውን መመልከት እንዳለባቸውም አሰልጣኙ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።



ከ23 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኑ አባላት በካፍ የልህቀት አካዳሚ ዝግጅታቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል፤

ቡድኑን በተቀላቀሉና ከተለያዩ ክለቦች ከተሰባሰቡ ተጫዋቾች ጋር በመሆንም ክፍተታቸውን ለመሙላት ዝግጅቱ አተኩሮ እየተሰራ ነው። የአቋም መፈተሻ ጨዋታዎችን በተመለከተ ቡድኑ ከሀገር ውስጥ ክለቦች ጋር የወዳጅነት ጨዋታዎች እያደረገ ሲሆን፤ ከካሜሩን ከ20 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድን ጋር ለመጫወት የሚያስችለውን ሙከራ እየተደረገ መሆኑንም አሰልጣኙ ገልጸዋል። የሚሳካ ከሆነም የተጫዋቾችን ወቅታዊ አቋም እንዲሁም የውድድሩን መንፈስ ለመመልከት መልካም አጋጣሚ እንደሚሆን አስረድተዋል።

እስካሁን ቡድኑን ካልተቀላቀሉት ተጫዋቾች መካከል አንዱ በደቡብ አፍሪካው ክለብ ማሜሎዲ ሰንዳውስ በመጫወት ላይ የሚገኘው አቡበከር ናስር ሲሆን፤ በቅርቡ ተመልሶ ከቡድኑ ጋር ዝግጅቱን ይቀጥላል በሚልም ይጠበቃል። ተጫዋቹ ካለው ልምድና ብቃት አንጻር ውጤቱን የተሻለ ለማድረግ እንዲሁም ለሌሎች ተጫዋቾች ተምሳሌት እንደሚሆንም አሰልጣኙ ተስፋቸውን ገልጸዋል።

የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ፍልሚያ የሚጠብቀው የኢትዮጵያ ከ23 አመት በታች ብሔራዊ ቡድን ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ጋር በሜዳው የሚያደርገው የመጀመሪያ ጨዋታ የፊታችን መስከረም 12 ይካሄዳል።

ብሔራዊ ቡድኑ የመጀመሪያ የደርሶ መልስ ጨዋታውን በሜዳው እንዲያደርግ በእጣ ማውጣት ሥነ-ሥርዓቱ መርሐ-ግብር ተይዞ የነበረ ሲሆን በሀገራችን በካፍ ፍቃድ ያገኘ ሜዳ አለመኖሩን ተከትሎ ጨዋታውን የሚያደርግበት ስታዲየም ጉዳይ አሳሳቢ ሆኖ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ከቀናት በፊት የወጡ መረጃዎች እንዳመለከቱት ብሔራዊ ቡድኑ የሜዳ ላይ ጨዋታውን በመዲናችን አዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስታዲየም እንዲያደርግ ፍቃድ አግኝቷል። በዚህም የመጀመሪያ ጨዋታውን መስከረም 12 በደጋፊው ፊት ሲያከናውን የመልስ ጨዋታውን ደግሞ መስከረም 17 ኮንጎ ላይ የሚከውን ይሆናል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የግል የቴክኖሎጂ አምራች ኩባንያዎች ለሳይበር ደሕንነት ያላቸው አስተዋፅኦ

**ይበል ካሳ**

የሳይበር ምህዳር ከነባራዊው ምህዳር የሚለይበት ዋነኛው ጉዳይ ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ነው። በዓለም ዙሪያ ያለገደብ የተሳሰረው የሳይበር ምህዳር የጥቅሙን ያህል የዚያኑ ልክ ያለገደብ ለጥቃት የተጋለጠ ሆኗል። ገንዘብ ለማግኘት፣ የራስን ፖለቲካዊ ግብ ለማሳካት፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለማድረስ፣ ሀገራዊ ቀውስ ለመፍጠር፣ ጠላቴ የሚሉትን አካል ለመበቀል፣ አለፍ ሲል ያልተገባ ዕውቅናና ዝና ለማግኘት ሳይበር የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ከመላው ዓለም ጥቃቶች ያለገደብ በቀላሉ ይፈጸማሉ። በመሆኑም ዓለም ከምንጊዜውም በላይ ለጥቃት፣ ለወንጀልና ለጦርነት ብሎም ለጥፋት ተጋላጭ ሆናለች።

በመሆኑም እነዚህን ጥቃቶች ለመከላከልና የሳይበር ምህዳሩን ለሰው ልጆችና ለዓለማችን አወንታዊ ዕድገት በሚበጅ መልኩ ለመጠቀም ደግሞ ከሁሉም በፊት ለደህንነቱ ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል፤ የምህዳሩና ምህዳሩ የሚሠራበት ቴክኖሎጂ ደህንነት ሲረጋገጥ ያኔ የእኛም ደህንነት ዋስትና ያገኛልና። ለዚህ ደግሞ ሦስቱ መሠረታዊ የሳይበር ደህንነት ምሰሶዎች መገንባትና መጠቀም አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። እነዚህም ሰው፣ መረጃና መሠረተ ልማትና መሥሪያ ቴክኖሎጂ ላይ የቆሙ ሲሆን ሰውና መረጃ ላይ የተመሠረተውን ከዚህ በፊት በሠራናቸው ጥንቅሮች አስቃኝተናችኋል። ዛሬ ተራውን ለመሥሪያ ቴክኖሎጂውና ቴክኖሎጂውን ለሚያመርቱት የግል ዘርፍ ኩባንያዎች አድርገናል።

የሳይበር ምህዳርን ከጥቃት በመጠበቅና የምህዳሩን ደህንነት በማረጋገጥ ሂደት ከሰውና ከመረጃ ቀጥሎ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ትልቁን ድርሻ ይይዛል። ምክንያቱም በአንድ ሀገር የሳይበር ምህዳር ውስጥ የሚዘረጉ ማናቸውም የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች ከምህዳሩ አሠራርና ደህንነት ጋር በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው በመሆናቸው ነው። ምክንያቱም ይላል በዮርዳኖስ የኢስራ ዩኒቨርሲቲ የሳይበር ደህንነት ተማራማሪው ያናል ኪላኒ፤ " አንድ መሰረተ ልማቶች በተገነቡና አንድ አዲስ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ በዋለ ቁጥር በሳይበር ምህዳሩ ላይ ይዞት የሚመጣው የራሱ የሆነ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ተያያዥ ስጋቶችንና የጥቃት ተጋላጭነቶችንም ጭምር ማስከተሉ አይቀሬ በመሆኑ ነው"።

ከዚህ አለፍ ሲልም በአንድ ሀገር ውስጥ የሚዘረጉ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች ዓይነትና ሥሪት በያንዳንዱ ተቋማት ውስጥ የሚኖረውን አጠቃላይ የሳይበር ምህዳር አሠራር ሁኔታና የሠራተኞቹን ግንዛቤ የሚወስኑበት ዕድል መኖሩንም ተመራማሪው ያመላክታሉ። ምክንያቱም ኮምፒውተር፣ በይነ መረብ፣ መረጃና መገናኛ እንዲሁም ቴሌኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን በዋናነት ከሚጠቀመውና በባህሪው እጅግ ተለጣጭ ከሆነው የሳይበር ምህዳር ጋር ደግሞ በአንድም ወይም በሌላ መንገድ የማይገናኝ የቴክኖሎጂ ውጤትና የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት የለምና ነው።

ከዚህ አኳያ እያንዳንዱ የመሥሪያ ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታና ግንባታ በአንድ ሀገር የሳይበር ምህዳር አጠቃላይ የአሠራር ሁኔታና በያንዳንዱ ግለሰብና ተቋማት የሳይበር ምህዳር አጠቃቀምና ደህንነት ላይ የጥቃት ተጋላጭነትን የማስከተል ዕድሉ እጅጉን የሰፋ በመሆኑ ጉዳዩን በከፍተኛ ትኩረት እንድንከታተለው የሚያስገድድ ይሆናል። ስለሆነም በሳይበር ምህዳሩ ውስጥ ማንኛውም የቴክኖሎጂ ምርት፣ መተግበሪያ ወይም ማንኛውም ጥቅም ላይ የሚውል የአገልግሎት ሥርዓት ሲበለፅግ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ሲሠራ በቅድሚያ ሊታሰብበት የሚገባ ትልቅ ጉዳይ የደህንነቱ ሁኔታ ሊሆን ግድ ይላል።

በመሆኑም አንድ የቴክኖሎጂ ምርት ዓላማ አድርጎ በተሠራበት የአሠራር ሂደት ተከትሎ ከሲስተሙ የሚመጡ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት መመሪያዎችን፣ ቅጾችን፣ ግብዓቶችን እንዲሁም መጠይቆችን በመከተልና ምላሾችን በመስጠት ተጠቃሚው የሚፈልገውን አገልግሎት በሚፈልገው ጊዜና ቦታ ያገኛል። በዚህ ሂደት ውስጥ እንደተጠቃሚ አገልግሎት ሰጪ ለሆነው ሲስተም ወይም ሥርዓት ግብዓቶችን በምናቀርብበት ጊዜ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የአሠራር ሂደት ከሲስተሙ ጋር በሚኖረን መስተጋብር ከቴክኖሎጂው ምርት አሠራር ጋር በተያያዘ ባልታወቀ ክፍተት ሲስተሙ ባልታለመለት መንገድ ጥቅም ላይ ሊውል ወይንም በአበልጻጊዎች የግል ፍላጎት የተነሳ ሆን ተብሎ ለደህንነት አደጋ የተጋለጠ ሆኖ ሊበለጽግ ስለሚችል ጥንቃቄን ይሻል። ስለሆነም አንድ የቴክኖሎጂ ምርት አገልግሎት ከመስጠቱ ባሻገር የደህንነቱ ጉዳይም እንዲሁ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

በዚህም ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊከሰት የሚችለውን የሳይበር ጥቃት ለመከላከልና ሊደርስ ከሚችለው አውዳሚ ጉዳት ለመዳን በያንዳንዱ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። ይህም ማለት መሠረተ ልማቱ ከመገንባቱና ቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ለሳይበር ጥቃት ከሚያጋልጡ ስጋቶች ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ከዚህ ቀደም የተዘረጉ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶችንም በየጊዜው ደህንነታቸውን መፈተሽ፣ የጥቃት ተጋላጭነታቸውን መለየት፣ ተጋላጭ ሆነው ሲገኙ ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ መውሰድና የሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ መንገዶችን ማዘመንና ማሳደግ ይገባል።

ለዚህ ደግሞ በሰለጠነ የሰው ኃይል ልማትና በመሠረተ ልማት ጥበቃ ዘመኑን የዋጀ የሳይበር ደህንነት አመራር መገንባትና መተግበር ቀዳሚ ሥራ ይሆናል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂ የተሟላ፣ ዘመኑ የደረሰበትን ውስብስብና ረቀቀ ሳይበር ጥቃት የሚመጥን ብቁና ዘመኑን የዋጀ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና የአሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ መዘርጋትና በቁርጠኝነት መተግበር እጅጉን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ ዘመኑን በሚመጥን መንገድ በቅርቡ ተሻሽሎ ተግባራዊ ከተደረገው የሀገሪቱ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ በተጨማሪ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አማካኝነት እየተጋጀ የሚገኘው "የኤሌክትሮኒክ መንግሥት የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ" መልካም ጅምር በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል እንላለን።

ፖሊሲው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኩል ለዜጎች፣ ለሠራተኞች፣ ለንግድና ለሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶችና የሚለሙ አገልግሎቶችን ደህንነታቸው በተጠበቀ መንገድ ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ መገለጹም ካነሳነው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ የሳይበር ደህንነት ችግሮችን በመከላከል ረገድ አንድ እርምጃ ወደፊት የተራመደ ነውና ሊበረታታ የሚገባው ጅምር መሆኑን ልንገልጽ እንወዳለን።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ